# የዜግነት ትምህርት የመምህራን መምሪያ

# 8ኛ ክፍል

## በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባነት ተዘጋጅቶ ተስማምቶ የተተረጎመ


### ተርጓሚዎች

1. አስመራ ቤጊ
2. ሞቲ ድንቁ
3. ፍራንኦል ዋቅጅራ
4. ኃይሉ ብሩ
5. አብደና አመኑ

### አርታዒዎች

1. እየሩሳሌም ገርባባ
2. ፈጠነ ቡልቻ
3. አሸብር ሀብታሙ
4. ሰለሞን ንጉሴ
5. ስሪቃ ገመቹ

**ግራፍክስ**

ታደሰ ድንቁ

**ገምጋሚ**

ደረጀ መኮንን ዴሬሳ

© ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014/2022

ይህ የተማሪዎች መጽሃፍ በኢፌዴሪ የትምህርት ምንስቴር አስተባባሪነት ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አሰተባባርነት ተስማምቶ ወደ አፋን ኦሮሞ የተተረጎመ ነዉ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

## ማዉጫ

ገጽ

ምዕራፍ አንድ፣ መልካምነት ...... 1
ይዘት1. የመልካምነት ፅንሰ ሃሳብ ...... 1
ይዘት2. የመልካምነት መርሆዎች ...... 5
ይዘት3. መልካምነት በተግባር ሲገለፅ ...... 15
ይዘት4. የመልካምነት አስፈላጊነት ...... 18
ይዘት 5. መልካምነት በተግባር ሲገለፅ/ በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ ...... 20
ምዕራፍ 2፡ ...... 22
መንግስት እና የመንግስት አስተዳደር ...... 22
ይዘት 1. የመንግስት አወቃቀር ...... 23
ይዘት 2. አሃዳዊ የመንግስት መዋቅር ...... 25
ይዘት3. የፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር ...... 27
ይዘት 4፡ ኮንፌዴራላዊ የመንግስት አወቃቀር ...... 31
ይዘት 5፡ የመንግስት ስርዓቶች ...... 33
ይዘት 6፡ ፓርላሜንታዊ የመንግስት ስርዓት ...... 35
ይዘት 7፡ ፕሬዝዳንታዊ የመንግስት ስርዓት ...... 37
ይዘት 8፡ ድብልቅ የመንግስት ስርዓት ...... 39
ይዘት 9፡ በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካከል ያለው ግንኙነት እና ልዩነት ...... 41
ይዘት 10፡ የኢትዮጵያ የመንግስት ስርዓቶች ...... 43
ይዘት 11: የኢትዮጵያ የመንግስት ስርዓቶች ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ...... 45
ምዕራፍ 3. ዴሞክራሲ ...... 50
ይዘት 1. የዴሞክራሲ ፅንሰ ሃሳብ ...... 50
ይዘት 2. መሰረታዊ የዴሞክራሲ መርሆዎች ...... 52
ይዘት.3 የዴሞክራሲ እሴቶች ...... 54
ይዘት4. የአገር በቀል የዴሞክራሲ ተቋማትና እስቶች አስፈላጊነት ...... 56
ይዘት 5. በኢትዮå ያ የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ እንቅፋቶችና እድሎች ...... 58
ምዕራፍ አራት፡ ሕገመንግስታዊነት (ክፈለግ 11) ...... 62
ይዘት 1 የህገመንግስት እና ህገመንግስታዊነት ፅንስ ሃሳብ ...... 62
ይዘት 2. የህገመንግስት አላማዎች ...... 64
ይዘት 3. የህገመንግስታዊ አስፈላጊነት ...... 66
ይዘት 4. የህገመንግስት አይነቶች እና ባህሪያት ...... 68

ይዘት 5 ሕገመንግስታዊነት ሰላምንና መረጋጋትን በማስፈን ረገድ ያለው ሚና ........ 71
ምዕራፍ 5፡ ሰብአዊ መብቶች ........ 74
ይዘት 1. የሰብአዊ መብቶች ዓይነቶች ........ 74
ይዘት 2. የእኩልነት መብት ........ 77
ይዘት 3. የሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ ክልሎች ሕገ መንግሥት ........ 79
ይዘት 4. በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ጥበቃ ተግዳሮቶች ........ 82
ይዘት 5. በኢትዮጵያ ውስጥ የሰብአዊ መብት ጥበቃን የሚያደናቅፉ ጉዳዮች ........ 84
ምዕራፍ 6፡ የግጭት አፈታት እና የሰላምግንባታ ........ 89
ይዘት1፤የግጭትና የሰላም ጽንሰ ሃሳብ ........ 89
ይዘት 2. የግጭት መንስኤዎች ........ 92
ይዘት 3. የግጭት አፈታት ........ 95
ይዘት 4. የግጭት አፈታት ስልቶች ........ 96
ይዘት 5. የሰላም ግንባታ ........ 99
ይዘት 6፡ግጭቶችን የሚፈቱ ሀገር በቀል ማህበራዊ ተቋማት ........ 101
ምዕራፍ 7፡ በጥልቀት የማሰብ እና የችግር አፈታት ክህሎት ........ 104
ይዘት1፡የችግር አፈታት ትርጉምና የህደቱ ደረጃዎች ........ 104
ይዘት2፡ በጥልቀት  የማሰብ ሂደት ደረጃዎችና ውሳኔ አሰጣጥ ........ 107
ይዘት3፡ በጥልቀት የማሰብና የችግር አፈታት ክህሎቶችና ባህርዎች አጠቃላይ እይታ ........ 109
ይዘት4፡ በጥልቀት የማሰብ ክህለቶችን የሚያሻሽሉ ዜዴዎች ........ 115
ይዘት5፡ ችግርን በመፍታት ሂደት ውስጥ በጥልቀት የማሰብ ችሎታ ጥቅሞች ........ 119
**የ8ኛ ክፍል የዜግነት ትምህርት ሲለበስ** ........ 123

## መግቢያ

በአንድ አገር ዕድገት ውስጥ ትምህርት የማይተካ ሚና አለው። በአገር ውስጥ ያለው የሰው ሃይል በዕውቀት፣በክህሎትና በስነ ምግባር የታነፀ ከሆነ የአገሩ የማደግ ዕድል የተቃና ይሆናል። ይህም ማለት የአንድ አገር ዕድገት በትክክለኛ መንገድ እንዲጓዝ ከተፈለገ የተማሩ ዜጎች ሚና ከፍተኛ ነው ማለት ነው ።

በአገሮች መካከል ያለው የዕደገት ልዩነት ለምሳሌ የምጣኔ ሀብት፣የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና የመሳሰሉት የልዩነቱ ዋና መንስኤ ለትምህርት በሚሰጡት ትኩረት ላይ የተመሰረተ ነው።

አገሮች ለትምህርት ትኩረት ከሚሰጡበት መንገድ አንዱ የትምህርት ፖሊሲ ሲሆን የአንድ አገር የትምህርት ፖሊሲ ዋና ትኩረቱ በክህሎት፣ዕውቀና በመልካም ስነ ምግባር የታነጹ ዜጎችን ማፍራት ነው። በዚህ መሰረት የግብረገብና የሰነ ዜጋ ትምህርት መልካም ባህሪይና ጥሩ ስነ ምግባር ያላቸው ዜጎችን ለማፍራት ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው።

ተማሪዎች የተለያየ ባህልና ዕምነት ባለው ህብረተሰብ ውስጥ እንዴት ተስማምተው መኖር እንዳለበቸው ለማስገንዘብ የግብረገብና የስነ ምግባር ትምህርት በጣም አስፈልጊ ነው። የተማሪዎችን የባህል ልዩነት ለመረዳትና አብሮ ለመኖር፣ የወቅቱን አገራዊና አለማቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ መረጃ እንዲኖራቸው፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለመገንዘብ እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የባህል ልዩነት አቻችሎና አስማምቶ ለመኖር የስነ ዜጋና የግብረገብ ትምህርት ዘርፈ ብዙ ጥቅም አለው።

በሌላ በኩል የግብረገብና የስነ ዜጋ ትምህርት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የባህል ልዩነት መረዳትና አብሮ ለመኖር ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡን ወግ፣ደንብና ባህል በመረዳት በህብረተሰቡ የልማት ስራ ውስጥ ጠንካራ ተሳትፎ ለማድረግ ያግዛል።

በተጨማሪም የማህበረሰቡን ባህሪይና ባህል ማወቅ ደግሞ ለሌላው አካል ያለንን አመለካከት ለማስታካከል ያግዛል። ራሳችንን ከማህበረሰቡ ባህል ጋር ለማቀናጀት ደግሞ ተማሪዎችን የግብረገብና የስነ ዜጋ ትምህርት ማስተማር ለነገ ህይወታቸው መሰረት ስለሆነ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ አመለካከታቸውን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲያስተካክሉ ያግዛቸዋል።ለምሳሌ ትምህርት ለሁሉም፣የትምህርትን አስፈላጊነትና የመሳሰሉትን በስረዓተ ትምህርት ውስጥ ማካተት ለወጣቶቹ በጣም አስፈላጊ ነው።

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለዜጎች መሰራታዊ እሴት ከሚባሉት ዋናው የግብረገብና የስነ ዜጋ ትምህርት ሲሆን ይህም በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ባህሎች፣ስረዓትና ደንቦችን በመረዳት አገራዊና አለማቀፋዊ አስተሳሰብ እንድናዳብር ያግዛል። በሌላ በኩል የስነ ዜጋና ግብረገብ ትምህርት የራስን ስሜት በመቆጣጠር የማስተዋል ክህሎታችን እንዲጨምር በማድረግ አስተዋይና ሁሉን አቀፍ አመለካከት እንዲኖረን ያደርጋል።የግብረገብና ስነ ዜጋ ትምህርት ለማስተማር ደግሞ አለም አቀፍ ወቅታዊ መረጃ ማግኘትና ይህንንም ክህሎት ማሳደግ በጣም አስፈላጊ ነው።

በሌላ በኩል በዕውቀት ላይ የተመሰረት ትክክለኛ ውሳኔ መወሰን መቻል፣መልሶ መላልሶ በጥልቀት ማሰብ፣የችግር መፍቻ ዘዴዎችን ማጎልበት፣አዲስ ፈጠራ መፍጠር፣ከህብረተሰብ ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር፣አብሮ መስራት፣እንዲሁም ዘመኑ የፈጠራቸውን ቴክኖሎጂዎች መጠቀም፣የማንነትና አለማቀፋዊነት የተካተተበት ትምህርት ማግኘት ለዜጎች ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም ይህ ስረዓተ ትምህርት ህብርተሰቡ በሰላም፣በተረጋጋና በመደጋገፍ መልካምና እውነተኛ ህይወት እንዲመራ ተማሪዎች የድርሻቸውን እንዲወጡ ወቅታዊ መረጃና አገራዊ የህትመት ስራዎችን ማግኝትና መጠቀም እንዳለባቸው ይገልፃል። እንዲሁም የፆታ እኩልነት፣የትምህርት ተደራሽነት፣ የአደጋ ግዜ ትምህርት፣የዐየር ንብረት ለውጥ፣ስለኤች አይ ቪ እና የመሳሰሉትን ትምህርቶች ያካትታል።

የዚህ ትምህርት ትኩረት አቅጣጫ በህብረተሰቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉና አገሪቷን ለችግር የዳረጉ ጉዳዮችን ለምሳሌ ስለ ሰላም፣ የሰላም ግንባታ፣ስለ አደንዛዝ ዕፅ፣የህብረተሰብ የጤና አጠባበቅ፣የመንገድ ደህንነትና ከዜጎች የሚጠበቀውን የግብርና ሥራ የመሳሰሉ ጉዳዮች እዚህ ትምህርት ውስጥ የተካተቱ ናቸው ።

## 1.1 የዜግነትና ግብረገብ ግብረገብ ትምህርት አላማ

የዜግነትና ግብረገብ ትምህረት ዋና አላማ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ዜጋ በመፍጠር የዴሞክራሲ ባህል የሚፈልገው ስረዓትና ደንብ እንዲሁም የዲሞክራሲ ስርዓት ለምሳሌ እንደ መቻቻልና ልዩነትን በውይይት የመፍታትን ባህል በማጎልበት ዴሞክራሲያዊ የሆነ ማህበረሰብ መፍጠር ነው።

በተጨማሪም ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ዜጎችን ማፍራት፣ለነፃነት፣ለዕኩልነት፣ ለፍትህና ክብር እንዲሁም የጋራ ማንነትን ለማጎልበት የሚታገሉ ዜጎችን ማፍራትን ያካትታል።

### 1.1.1 1 የዜግነትና ግብረገብ ትምርረት ጥቅልና ዝርዝር አላማዎች

**የዜግነትና ግብረገብ** ትምህርት ጥቅል አላማ መልካም ዜጋ፣ ጥሩ ስነ ምግባር ያለው፣ በዕውቀትና በክህሎት የዳበረ እንዲሁም በመልካም እሴቶች የተገነባ ዜጋን ማፍራት ሲሆን ይህም በአገራዊ ጉዳይ ማለትም በኢኮኖሚ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ በንቃት የሚሳተፍ ዜጋን ማፍራት ነው።

### 1.1.2 የዜግነትና ግብረገብ ትምህርት ዝርዝር አላማ

**የዜግነትና ግብረገብ ትምህርት ዝርዝር አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣**

- መግባባትን፣መረዳዳትን፣መቻቻልን፣ልዩነትንና ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህልን ለማጎልበት፣
- የህብረተሰቡን ባህሪይ ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን በዕውቀትና ሞራላዊ እሴቶች ላይ ለመገንባት፣
- የአገር ፍቅር ስሜትና ሃገራዊ የመግባባት ባህልን ለማጎልባት፣
- የህብረተሰቡን ሞራላዊ እሴትና ስነ ምግባር ለማዳበር፣
- በልዩነት ውስጥ ያለውን አገራዊ አንድነት ዕውቅና ለመስጠት፣
- በጥልቀት ማሰብን መቻቻልን አብሮ በሰላም መኖርን በተግባር ማሳየት፣
- ሃገር በቀል ዕውቀቶችን በመጠቀም ግጭትን የመፍታት ክህሎትን ማሳደግ ናቸው።

## ለመምህሩ ማስታወሻ

ይህ የመምህር መምሪያ መጽሃፍ የተዘጋጀው የስምንተኛ ክፍል ስነ ዜጋ ትምህርት የሚያስተምረው መምህር በትምህርቱ ውስጥ ያሉትን ሃሳቦች ለመረዳት እንዲያግዘው ተብሎ ነው። በዚሁ መሰረት ተማሪዎቹ ዕውቀት፣ችሎታ፣ክህሎት እንዲሁም ብቃት አግኝተው በህብረተሰቡ የልማት ሥራ ላይ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ መምህሩ ተማሪዎቻቸውን በቂ ዕውቀት እንዲያስጨብጧቸው ታስቦ የተዘጋጀ አጋዥ መጽሃፍ ነው። በተጨማሪም ይህ የመምህሩ መምሪያ ተማሪዎች መማር ያለባቸውን ርዕስና የመማር ማስተማር አቅጣጫን ያሳያል።

ይህ የመምህሩ መምሪያ የትምህርት መርጃ መሳሪያና ለትምህርቱ ዕገዛ የሚውሉ ቁሳቁሶችን ተማሪዎች ከአካባቢያቸው በሚገኘው ነገር በነፃነት እንዲያመርቱና እንዲጠቀሙ ያበረታታል። በተጨማሪም በክፍል ውስጥ መምህሩ/ሯ እያንዳንዱን ርዕስ እንዴት እንደሚያስተምሩ ያመለክታል።ይህም በመጀመሪያ ጠቅላላ ሃሳብና ከተማሪው የሚጠበቀውን የመማር ብቃት ይገልፃል።በመቀጠል ለእያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት ከተማሪው የሚጠበቀውን ዝቅተኛ የመማር ብቃት፣የክፍለ ትምህርቱ አላማ ፣ለትምህርቱ አግዥ የሆኑ መፃህፍትና ተጨማሪ መረጃዎችን ይገልፅና የዕለቱን ትምህርት በአነቃቂ ጥያቄዎች በመጀመር የሚሰሩ ተግባራትንና መልመጃዎችን ያካትታል።
ባጭሩ ይህ የመምህሩ/ሯ መምሪያ መፅሃፍ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ካለው ፅንሰ ሃሳብ ጋር እንዲስማማ ተደርጎ የተዘጋጀና ለመምህሩ አቅጣጫ አመልካች ሆኖ በተጨማሪም በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አስፈላጊና ጠቃሚ መረጃዎች የያዘ ነው፡፡

### 1.1.2 ይህ የመምህር መምሪያ መጽሃፍ የተዘጋጀው

**መምህሩ/ሯ፡-**

- የስምንተኛ ክፍል የዜግነት ትምህርትን ጠቅላላ ዓላማና የምዕራፎቹን አጠቃላይ ውጤትና ዝቅተኛውን የተማሪ የመማር ብቃት እንዲለዩ፣
- ዓመታዊና ሳምንታዊ ዕቅዶችን እንዲያዘጋጁ፣
- ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ቁሳቁሶችን ከአከባቢያቸው እንዲያዘጋጁና እንዲጠቀሙ፣
- ለማስተማር አመቺ የሆኑ ስልቶችን በመምረጥ እንዲጠቀሙ፣
- በቂ ጊዜ በመውሰድ የትምህርት እቅድ እንዲያወጡ፣

- አጋዥ የመማሪያ ቁሳቁሶችን በክፍል ውስጥ እንዲያዘጋጁ፣
- አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት የመገምገሚያ ስልቶችን እንዲያዘጋጁና፣
- ከአዲሱ የስምንተኛ ክፍል ስርዓተ ትምህርት ዓላማ ጋር እንዲያዛምዱ ለማስገዘብ ነው።

### 1.3 የመምህሩን መምሪያ ማቀናበር

የስምንተኛ ክፍል የስነ ዜጋ ትምህርት ከሰባተኛ ክፍል የቀጠለ ሲሆን ተማሪዎች የተፈለገው ደረጃ ላይ እንዲደርሱና ለክፍሉ የተመደበው የትምህርት ዓላማ ውጤታማ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

**የዜግነት ትምህርት** እንደ ሌሎቹ የትምህርት ዓይነቶች ሁሉ በተለያየ አቀራረብ ሊቀርብ ይችላል። ይሁን እንጂ የስነ ዜጋን ትምህርት ልዩ የሚያደርገው ትምህርቱ በህብረተሰቡ የዕለት ተዕለት ህይወት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ከህብረተሰቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ማግኘት ስለሚችሉ የተማሪዎችን የተግባር ክንውንና ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑ ነው። በተጨማሪም ከዚህ በታች የቀረቡት ሃሳቦች የስነ ዜጋ ትምህርትን በትክክል ለማቀድ፣ለማቅረብና ለመገምገም የሚረዱ ናቸው ተብለው ይታመናሉ።

### ቅድመ ዝግጅት

ይህ ክፍል የዜግነት ትምህርትን ስራ ላይ ለማዋል ወሳኙ ክፍል ነው። በዚህ መሰረት የትምህርት እቅድን ለማዘጋጀት ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ተግባራትን ማቀናበርን ይጠይቃል። በዚህ ደረጃ መምህሩ/ሯ በደንብ መዘጋጀት፣ማንበብ፣የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን ፣ዝጋጀት፣ የትምህርት ዕቅድን ማዘጋጀትና በደንብ ተዘጋጅቶ ክፍል መግባት ይጠበቅበታል።

## በትምህርት ወቅት የሚከናወኑ ተግባራት

በዚህ ወቅት የመማር ማስተማር ሂደት የሚጀመርበት ሲሆን የእርስዎ ሃላፊነት በትምህርቱ ዓላማ ላይ ማብራሪያ መስጠት፣ የሚሰሩ ተግባራትን ማቀናበርና ለተማሪዎች የሚፈለገውን ዕገዛ ማድረግ ነው።

## መረጃ ማጠናከርና ማጠቃለያ መስጠት

በመማር፣ማስተማር ሂደት ውስጥ የመጨረሻው ክፍል መረጃ መሰብሰብና ማጠቃለያ መስጠት ነው።ይህም የምዕራፉ ማጠቃለያና የትምህርቱ ዓላማ ምን ያህል ከግብ እንደደረሰ ለመለየት የሚረዳ ሲሆን የተለያዩ ጥያቄዎችና የሚሰሩ ተግባራትን አጠቃሎ የያዘ ነው።

# ምዕራፍ አንድ፤ መልካምነት

**ለዚህ ምዕራፍ የተመደበው 18 ክፍለ ጊዜ ነው፡፡**

ይህ ምዕራፍ የመልካምነትን ፅንሰ ሃሳብና መርሆዎች አስፈልጊነት ላይ ያተኩራል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተለያዩ ውስን ጥናቶች/ታሪኮች የቀረቡ ሲሆን ይህም ለመልካም ተግባራት ምሳሌ የሚሆኑ ሃሳቦች በስፋት ቀርበዋል። በተጨማሪም ለርዕሶቹና ለንዑሳን ርዕሶቹ የተሰጠው ማብራሪያ በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ መልካምነትን በተግባር ለማሳደግ የሚያግዙ ናቸው። ስለዚህ በትምህርቱ ማጠቃለያ ተማሪዎች በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ መልካም ተግባራትን ስራ ላይ በማዋል የህብረተሰቡን ደስታ ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል ተብሎ ይታሰባል።

| ከተማሪው የሚጠበቁ ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች | ርዕሶች |
|---|---|
| ➢ የመልካምነትን ፅንሰ ሃሳብ ያብራራሉ፤ | 1.1 የመልካምነት ፅንሰ ሃሳብ |
| ➢ የመልካምነት መርሆዎች ይገልፃሉ፤ | 1.2 የመልካምነት መርሆዎች |
| ➢ የመልካምነትን አስፈላጊነት ያብራራሉ፤ | 1.3 የመልካምነት አስፈላጊነት |
| ➢ በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ መልካምነትን በስራ ይተገብራሉ። | 1.4 መልካምነት በተግባር ሲገለፅ |

## ይዘት1. የመልካምነት ፅንሰ ሃሳብ

በዚህ ርዕስ ስር ከተማሪው የሚጠበቁ ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች

ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- የመልካምነትን ፅንሰ ሃሳብ ይዘረዝራሉ፤
- የመልካምነትን ትርጉም ይሰጣሉ፤
- መልካምና መጥፎ ባህሪያትን ይለያሉ፤
- የስነ ምግባርን ምንነት ይገልፃሉ፤
- ስነ ምግባርና መልካምነት ያላቸውን ግንኙነትን ያብራራሉ፡፡

| ጉዳይ | የትምህርት ቁሳቁስና የሚሰሩ ተግባራት |
|---|---|
| 1 የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ | ጥቁር ሰሌዳ፣ቻርት፣የተማሪው መጽሃፍ፣እስክርቢቶና የመፃፊያ ወረቀት |
| 2 የመማር ማስተማር ዘዴ | ጥያቄ መጠየቅ፣የቡድን ስራና የተግባር ክንውን |
| 3 አባሪ መፃህፍት | መጽሃፍ፣በመልካምነት ላይ የተፃፉ የተለያዩ ጽሁፎች፣የተለያዩ የህትመት ስራዎች |

**መግቢያ**

ይህ ክፍለ ትምህርት መልካምነት እና ስነ ምግባር ላይ ያተኩራል። መምህሩ በመጀመሪያ የዕለቱን ትምህርት ርዕሰ በጥቁር ሰሌና ላይ በመፃፍ ተማሪዎቹ በማስታወሻ ደብተራው ላይ እንዲፅፉ ያደርጋል። በመቀጠልም የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎቹ ስለ መልካምነት መገንዘባቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል። በዚሁ መሰረት መልካምነት ከስነ ምግባር መርሆዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በሃሳብ ወይም በተግባር ሊገለፅ እንደሚችል ተማሪዎቹን ያስገነዝባቸዋል። በሌላ በኩል ስነ ምግባር ማለት መልካምና መጥፎ ባህሪያትን መለየት ወይም በህብረተሰቡ ውስጥ ትክክል የሚባሉና የማይባሉ ጉዳዮችን የሚያጠና ትምህርት ሆኖ በህብረተሰቡ የኑሮ ሂደት ውስጥ መልካም የሆነና ያልሆነውን ሃሳብ ወይም ተግባርን የምንለይበት የትምህርት ዓይነት ነው፡፡

**መልካምነት**

ከሶስቱ የፍልስፍና ዘርፎች አንዱ መልካምነት ነው። መልካምነት ማለት ጥሩ ተግባራትን ወይም ባህሪያትን የሚያመለክት ሲሆን የሰዎች ስራ ሁሉ በስነ ምግባር ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት የሚገልፅ ትምህርት ነው። ስለዚህም በህብረተሰቡ ውስጥ መቻቻል፣አብሮ መኖር፣መረዳዳት እና የመሳሰለው ባህል እንዲዳብር የመልካምነትና ስነ ዜጋ ትምህርት ትልቅ ድርሻ አለው።

በሌላ በኩል ከሶስቱ የኖርማቲቭ አጠናን ዘዴዎች አንዱ መልካምነትን ማበረታታት ሲሆን በጥንት ዘመን የነበረው የመልካምነት ፅንሰ ሃሳብ የግለሰቦችን ባህርይ ማጥናት ላይ ያተኮረ ነበረ።ይሁን እንጂ ከግለሰብ ባህሪይ ይልቅ መልካምነትን በተግባር መተርጎም የወቅቱ የኖርማቲቭ አጠናን ዘዴ ትኩረት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

**በክፍለ ትምህርቱ ጊዜ የሚሰሩ ተግባራት፣ የቡድን ስራና ውስን ጥናቶችን ማሰላሰል**

1.የዕለቱን ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎችን በቡድን በቡድን ከፋፍሏቸው። ተማሪዎቹን በቡድን የመከፋፈል ዋና አላማው የተወሰነ ቡድን መልካም፣የተቀረው ደግሞ የመጥፎ ባህሪያትን ምሳሌ በተግባር ክንውን እንዲያሳዩ ታስቦ ነው።በዚሁ መሰረት አራቱ ቡድን መልካም ስነ ምግባርን አራት ቡድን ድግሞ በተቃራኒው የመጥፎ ስነ ምግባርን ሃሳብ እንዲዘረዝሩ አድርጓቸው። በመቀጠልም ለተማሪዎች የተወሰነ ጊዜ ስጧቸውና በሃሳብ የተዘረዘረውን በተግባር እንዲያሳዩ አድርጓቸው።

ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹ የተሰማቸውን ሃሳብ እንዲያቀርቡ ይሁን።ከዚያም ተማሪዎቹ የሰጡትን ሃሳብ በማቀናጀት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉላቸው።ይህም ተማሪዎቹ የመልካምነትን መርሆዎችና ተቃራኒ የሆኑ ጉዳዮችን እንዲለዩ ይረዳቸዋል።

በዚህ ሂደት ውስጥ ተማሪዎቹ የመልካምነትመርሆዎችን መረዳታቸውን ለማወቅ፣

- የስነ ምግባር መርሆዎች መኖራቸውን ለመረዳት፣ ማንኛውም ሰው ለመልካምም ይሁን ለመጥፎ ሃሳብና ድርጊት ሃላፊነት እንዳለብት መገንዘብ ያስፈልጋል።

በተማሪው መጽሃፍ መልመጃ አንድ ውስጥ የተጠየቀው ጥያቄ ተማሪዎቹ ከዚህ በታች ባለው ምሳሌ መሰረት ሊመልሱ ይችላሉ።

| ተ/ቁ | መልካም ሃሳብ/ ተግባር | መጥፎ ሃሳብ/ተግባር |
|---|---|---|
| 1 | ታማኝነት | ወላዋይነት |
| 2 | ፍትሃዊነት | ኢፍትሃዊነት |
| 3 | ለሰው መልካም አሳቢነት | ለሰው ክፉ አሳቢነት |
| 4 | ታላላቅ ሰዎችን ማክበር | ታላላቅ ሰዎችን አለማክበር |

2. በተማሪው የመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ስለ **ቀበሮና የፍየል ሙክት** የሚያወሳ ታሪክ ቀርቧል። ይህን የጉዳይ ጥናት/ታሪክ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች አንብቡላቸው።ከዚህ የጉዳይ ጥናት ተማሪዎቹ ምን እንደ ተገነዘቡ ጠይቋቸው። በዚህ ታሪክ ውስጥ የቀበሮዋ ተግባር ጥሩ ነው ወይስ መጥፎ ነበር? ለምን? ይህንን ታሪክ በተመለከተ አጥጋቢ የሆነ

ሃሳብ ለተማሪዎች ስጧቸው።የቀበሮዋን ተግባር እንደ ምሳሌ በመውሰድ ለተማሪዎቹ የማጠቃለያ ሃሳብ ስጧቸው።

**ክለሳ**

እንደ ሌላው ትምህርት ሁሉ ለዚህም ክፍለ ትምህርት የቃል ጥያቄና የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎቹን መገምገም ይችላሉ።እነዚህ የግምገማ ጥያቄዎች ደግሞ የትምህርቱ አላማ ምን ያህል ከግብ እንደ ደረሰ ለመረዳት ያግዙዎታል።

- ተማሪዎቹ የትኛውን የመማርያ ዘዴ ወደዱት?
- በይበልጥ ማንበብን፣መፃፍን ወይስ የቃል ጥያቄዎችን?
- ይህ ለምን እንደሆነ መግለፅ ትችላለህ/ሽ?
- አጠቃላይ ተግባራትን በተመለከተ የተማሪዎቹ በራስ መተማመን እንዴት ነበር?
- ተማሪዎቹ በቡድን ወይም በጥንድ ያለውን ስራ ወደዱት?
- በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎቹ የተሰላቹበት ነጥብ/ጉዳይ አለ?

**በተጨማሪም**

ተማሪዎቹ የመልካምነትን ፅንሰ ሃስብ እንዲያስታውሱት ጥያቄ ጠይቋቸው። የተማሪዎቹን ውይይትና የሰሩትን የተግባር ክንውን በመመልከት ብቃታቸውን መዝግቡ።እያንዳንዱ ተማሪ የግልና የቡድን ስራዎችን እንዴት እንደከወነ በመገምገም ግብረ መልስ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ።

**ስነ ምግባር**

ይህ ክፍለ ትምህርት የመልካምነትን ፅንሰ ሃሳብ፣ስነ ምግባር፣የስነ ምግባርና መልካምነት ግንኙነትና የመሳሰሉ ነጥቦች ላይ ያተኩራል።መምህሩ ተማሪዎቹ የመልካምነትን ፅንሰ ሃሳብ፣መልካምና መጥፎ ተግባራትን ለይተው መረዳታቸውን ማወቅ ይጠበቅብዎታል።

ሰነ ምግባር ማለት የስረዓትና ደንቦች አካል ሆኖ በህብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸውን ሃሳብና ተግባር የሚያመለክት ነው። መጥፎ ሁሌም የመልካም ተቃራኒ ሆኖ በህብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት የሌላቸውን ሃሳብና ተግባር የሚያሳይ የህብረተስቡን ባህል የሚቃረን የመልካምነት ተቃራኒ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

# ይዘት2. የመልካምነት መርሆዎች

በዚህ ርዕስ ውስጥ ከተማሪው የሚጠበቁ ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች

ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- እያንዳንዱን የመልካምነት መርሆ ለይተው ይረዳሉ፤
- የመልካምነት መርሆዎችን ይዘረዝራሉ፡፡
- የመልካምነት መርሆዎችን አስፈላጊነት ይገልፃሉ፡፡

| | ጉዳይ | የመማሪያ ቁሳቁስና የሚሰሩ ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ | ጥቁር ሰሌዳ ፣ ቻርት ፣የተማሪው መጽሃፍ እስክርቢቶና ወረቀት |
| 2 | የመማር ማስተማር ዘዴ | የቃል ጥያቄ፣ የቡድን ስራና የተግባር ክንውን |
| 3 | አባሪ መጽሃፍ | መጻሕፍት፣ በመልካምነት ላይ የተፃፉና ተያያዥነት ያላቸው አንቀፆች፣ የተለያዩ ጽሁፎች፣ |

**መግቢያ**

ይህ ክፍለ ትምህርት ስለ ስነ ምግባር፣የመልካምነት መርሆዎች የሆኑትን እንደ ታማኝነት፣ ፅናት/ቆራጥነት፣ርህሩህነት፣ለጋስነት፣ፍትሃዊነት፣ስነ ምግባር፣አስተዋይነት የሚባሉ ነጥቦች ላይ ያተኩራል። የዚህ ክፍለ ትምህርት ዓላማም ተማሪዎቹ እነዚህን የመልካምነት መርሆዎች ተገንዝበው በዕልት ተዕለተ ህይወታቸው ውስጥ በመተግበር የባህሪይ ለውጥ እንዲያመጡ ታስቦ ነው።

ባለፈው ወቅት የተማሩት ትምህርት ላይ በመመስረት ስነ ምግባርና መልካምነት ያላቸውን ዝምድና ለተማሪዎቹ በማስታወስ የዕለቱን የትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመፃፍ ተማሪዎቹ በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ያድርጉ።መልካምነት በህብረተሰቡ የሞራል እሴትና ስነ ምግባር ላይ የሚገነባ ሲሆን የመልካምነት መርሆዎች ከሚባሉት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉ ናቸው።

1. ታማኝነት

ታማኝነት የገቡትን ቃል ማግበር፣ሃላፊነትን መወጣት፣እውነተኛና ፍትሃዊ የሆነ ስራ መስራት፣ ቅን መሆን፣ ታማኝነት ከሚገለፅባቸው ባህሪይዎች ውሰጥ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ

የታማኝነት ባህሪይ መዳበርና መጎልበት ከሰዎች ዕምነትና ተወዳጅነት እንድናገኝ ይረዳናል። በጓደኞቻቸው ዕምነት የሚጣልባቸው ሰዎች በተመሳሳይ ከህብረተሰቡም ዕምነት ያገኛሉ።በመሰረተ ሃሳብ ደረጃ ታማኝነት ለራስ ወይም ለሰው ሊሆን ይችላል።

**የመረዳት ጥያቄ አራት፣ ከላይ ከተጠቀሰው የጉዳይ ጥናት ምን ትገነዘባልህ?**

በተማሪው የመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የልጇት እናት ለአማቿ ዕቃ ቋጥራ እንዲሸጥላት ገበያ መላኳ በጉዳይ ጥናት መልክ ቀርቧል። ይህንን ታሪክ በክፍል ውሰጥ ለተማሪዎቹ አንብቡላቸው። ከዚያ በኋላ ተማሪዎቹ ከጉዳይ ጥናት ምን እንደተገነዘቡ ጠይቋቸው። በዚህ የጉዳይ ጥናት ውስጥ አማች/ የልጇት ባል ያደረገው ተገባር ጥሩ ነው? ወይስ መጥፎ? ይህንን ታሪክ በተመለከተ የተማሪዎችን የመረዳት ችሎታ ለማወቅ ጥያቄ ይጠይቁና ብቃታቸውን መዝግቡ። በጥቅሉ አማች/ የልጅት ባል የፈፀመውን ዕምነት ማጉደል እንደ ምሳሌ በማንሳት ለተማሪዎቹ የማጠቃላያ ሃሳብ ይስጡ።

**የሚሰሩ ተግባራት፣ የግል ተሳትፎና የቡድን ስራ**

1.እያንዳንዱ ተማሪ ታማኝነትን በተመለከተ የራሳቸውን ፍቺ እንዲፅፉና ከጓደኞቻቸው ጋር ሃሳብ እንዲቀያየሩ አድርጓቸው። በትምህርት ሂደት ውስጥ ዕገዛ የሚፈልግ ተማሪ ካለ አስፈላጊውን ዕገዛ አድርጉላቸው። እያንዳንዱ ተማሪ ለታማኝነት የሰጠውን ፍቺ በመሰብሰብ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉላቸው። በተጨማሪ ተማሪዎቹ ታማኝነት ለራስ፣ ለጓደኛና ለህዝብ ያለውን ጠቀሜታ ሃሳብ እንዲቀያየሩ አድርጉ። ተማሪዎች በጥልቀት እንዲያስቡ ጊዜና ዕድል ስጧቸው። እንዲሁም መልሶቻቸውን በክፍል ውሰጥ እንዲያቀርቡ አድርጉ። በመጨረሻው በጣም አስፈላጊ የሆነውን ነጥብ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ የተማሪዎችን ሃሳብ አጠቃሉ።

2..ተማሪዎቹ በጥንድ በጥንድ በመሆን ታማኝ መሆን ያለው ጥቅምና ታማኝ አለመሆን ያለውን ጉዳት በሚመለከት ሃሳብ እንዲቀያየሩ ይሁን።ታማኝ መሆን በትምህርት ቤት ጓደኛና ህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ጥቅም ተማሪዎቹ እንዲወያዩበትና በተግባር እንዲከውኑ አድርጉ። የተማሪዎቹ የተግባር ክንውን ዋና ዓላማው ታማኝነትን ከዕለት ተዕለት ህይወታቸው ጋር እንዲያያይዙት ለማበረታታት ነው። ለምሳሌ ፈተና መስረቅ፣ገንዘብ ከጓደኛና ከቤተሰብ ደብቆ መውሰድ፣ መዋሸት ወይም መጥፎ ተግባር መፈጸም ዕምነት የሚያሳጣ ድርጊት መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

3. አሁንም ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ በተለያየ ቡድን እንዲከፋፈሉ ይሁን።ከተቻለ አቀማማጣቸው ባሉበት ወይም በዴስክ መልክ ይሁን።የዚህ ዓላማ የዕለቱ ትምህርት ለተማሪዎቹ አመቺ እንዲሆን ታስቦ ነው። በተጨማሪም በህብረተሰቡ ውስጥ ታማኝነት ያለውን ጥቅም ለማወቅና በስራ ለመተርጎም የተማሪዎቹን የመከወን ችሎታ ለማረጋገጥ ነው።

በመጨረሻም የተማሪዎችን ውይይትና ሃሳብ በማቀናበር የተሻለውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ የማጠቃለያ ሃሳብ ስጧቸው።

**ክለሳ**

እንደ ሌላው ክፍለ ትምህርት ሁሉ ለዚህም ትምህርት የቃል ጥያቄና የቤት ስራ በመስጠት መገምገም ይችላሉ። የግምገማው ዋና ጥቅም ተማሪዎቹ ትምህርቱን ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅ ነው። ይህም ትምህርቱ ለታሰበለት ዓላማ መድረሱን ለመገምገም የሚያግዝ ነው።

- ተማሪዎቹ የትኛውን ትምህርት ወደዱት/መረጡት?
- ማንበብን፣መፃፍን ወይስ የቃል ጥያቄዎችን?
- ይህ ለምን እንደሆነ መግለፅ ትችላለህ/ሽ?
- የተማሪዎችን የተግባር ክንውን በተመልከተ የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ምን ያህል ነበር?
- ተማሪዎቹ በግል፣በጥንድ፣በቡድን የተከናወኑ ስራዎችን ምን ያህል አብረው ሰርተዋል?
- በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ የሰለቹበት ነጥብ/ጉዳይ አለ?

**በተጨማሪም**

ተማሪዎቹ እንዲያስታውሱ የታማኝነትን አስፈላጊነት ጠይቋቸው። የተማሪዎችን ወይይትና ተግባራት በመከታተል ብቃታቸውን መዝግቡ። እያንዳንዱ ተማሪ የግል ተግባራትና የጉዳይ ጥናቶችን ለመስራት ያሳዩትን ሙከራ በመገምገም ማጠቃለያ ሃሳብ ስጧቸው።

**2..ፅናት/ቆራጥነት**

ከመልካምነት መርሆዎች ውስጥ ሌላኛው ፅናት ሲሆን ባለፈው ክፍለ ትምህርት በመልካምነት ፅንሰ ሃሳብ ውስጥ የታማኝነትን ጥቅም መማራቸውን ተማሪዎቹን አስታውሷቸው። በመቀጠል የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ለይ በመፃፍ ተማሪዎቹ በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ አድርጉ።

**ቁልፍና የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

ፅናት/ቆራጥነት ማለት ምን ማለት ነው?

አንድን ስራ በፅናት መስራት ያለው ጥቅም ምንድነው?

ተማሪዎቹ ከላይ የተጠቀሱትን የማነቃቂያ ጥያቄዎች እንዲወያዩበት አድርጉ። የተማሪዎችን የውይይት ሃሳብና የሙከራ መልስ በሰሌዳ ላይ በመፃፍ የፅናትን ጥቅምና አስፈላጊነት ለተማሪዎቹ ማብራሪያ ስጡ።

**የሚሰሩ ተግባራት፣የጉዳይ ጥናትን ማሰላሰልና የተግባር ክንውን**

1. ለመከታተል በሚያመችዎት ሁኔታ የክፍል ተማሪዎቹን በቡድን በቡድን ክፋፍሏቸው። ተማሪዎቹን በቡድን የመከፋፈል ዓላማው በጥናቱ ውስጥ የተጠቀሰውን የኮሎኔል አብዲሳ አጋን ታሪክ በቡድን እንዲወያዩበት ለማድረግ ታስቦ ነው። በመቀጠልም ከታሪኩ የተረዱትን እንዲወያዩና ሃሳብ እንዲቀያየሩ ፍቀዱላቸው። ተማሪዎቹ ሃሳብ በሚቀያየሩበት ወቅት የተቸገሩበት ጉዳይ ካለ አግዟቸው። በመጨረሻም የተማሪዎቹን ግብረ መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ የማጠቃለያ ሃሳብ መሰጠት ይችላሉ።

2.አሁንም ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ በተለያየ ቡድን እንዲከፋፈሉ ይሁን።ከተቻለ እንደ አቀማመጣቸው ባሉበት ወይም በዴስክ መልክ አድርጉ። በመቀጠል ተማሪዎቹ እንዴት በግል ህይወታቸው ፅናትን መተግበር እንደሚችሉ አስረዱዋቸው። በመጨረሻም ፅናትን የሚያበረታቱ ሃሳቦችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎቹ የተፃፈውን በተግባር እንዲከውኑ ጊዜ ስጧቸው።

3. በተጨማሪም የኮሎኔል አብዲሳ አጋን ታርክ ተማሪዎቹ በዕረፍት ጊዜያቸው በክፍል ውስጥ እንዲከውኑት ፍቀዱላቸው።ተማሪዎቹ የተግባር ክንውን በሚሰሩብት ጊዜ ልምድ

እንዲለዋወጡ ይሁን። ተማሪዎቹን የተግባር ክንውን የማሰራቱ ዋና ዓላማ ዕናትን በህይወት ሂደት ውስጥ እንዲተገብሩ ለማበረታታት ታስቦ ነው።

**ክለሳ**

ይህንን ክፍለ ትምህርት ተማሪዎችን በቃል ጥያቄ መገምገም ይችላሉ። የግምገማው ዋና ጥቅም ተማሪዎቹ ትምህርቱን ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅ ነው። ይህም የትምህርቱ ዓላማ ከግብ መድረሱን ለመገንዘብ የሚያግዝ ዘዴ ነው።

- ተማሪዎቹ የትኛውን ትምህርት ወደዱት/መረጡት?
- ማንበብን፣መፃፍን ወይስ የቃል ጥያቄዎችን?
- ይህ ለምን እንደሆነ መግለፅ ትችላለህ/ሽ?
- የተሰሩ ተግባራትን በተመልከተ የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ምን ያህል ነበር?
- ተማሪዎቹ በጥንድ፣በቡድን የተከናወኑ ስራዎችን ምን ያህል አብረው ሰርተዋል?
- በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ የሰለቹበት ነጥብ/ጉዳይ አለ?

**በተጨማሪም**

ለማስታወስ እንዲረዳቸው ዕናት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎችን ጠይቋቸው። በተጨማሪም የዕናትን ጥቅም ይጠይቁ።ተማሪዎቹ ዕናትን በተግባር ለመግለፅ በሚሞክሩበት ጊዜ ሙክራዎቻቸውንና ብቃታቸውን መዝግቡ።እያንዳንዱ ተማሪ የግል ተግባራትና የጉዳይ ጥናቶችን ለመስራት ያሳዩትን ሙከራ በመገምገም ማጠቃለያ ሃሳብ ስጧቸው።

**3.ርህሩህነት**

ከመልካምነት መርሆዎች ውስጥ ሶስተኛው ርህሩህነት ነው። ከዚህ ክፍለ ትምህርት በፊት ስለ ዕናትና የዕናትን አስፈላጊነት መማራቸውን ለተማሪዎቹ ማስታወስ አስፈላጊ ነው።

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

**ርህሩህነት ማለት ምን ማለት ነው?**

ተማሪዎቹ ከላይ የተጠቀሱትን የማነቃቂያ ጥያቄዎች እንዲወያዩበት ጊዜ ስጧቸው። የተማሪዎችን የሙከራ መልስ በሰሌዳ ላይ በመፃፍ የፅናትን ጥቅምና አስፈላጊነት ለተማሪዎቹ ማብራሪያ በመስጠት ወደ ዕለቱ ትምህርት መግባት ይችላሉ።

ርህሩህነት ማለት የሰዎችን ችግር የመረዳትና የመፍትሄው አካል ለመሆን መዘጋጀት ወይንም የሰው ልጆችን ችግር ለመፍታት ቀና ሃሳብና ተግባር ማሳየት ማለት ነው። ይህም ለሰው ማሰብ፣የተቸግሩትን መርዳት፣የሰዎችን ችግር እንደ ራስ ችግር ማየት፣የሰዎችን ስሜት መገንዘብ፣የተቸገሩትን መረዳትና የመሳሰሉትን ያካትታል። በሌላ በኩል ርህሩህነት ማለት የሰዎችን ችግር መገንዘብ ብቻ ሳይሆን ለመፍትሄው መታገልና የመፍትሄው አካል መሆንን ይጨምራል።

**የሚሰሩ ተግባራት፣ የተግባር ክንውን**

1. ክፍለ ትምህርቱን ለመከታተል በሚያመች ሁኔታ ተማሪዎቹን በቡድን በቡድን ይከፋፈሉ።ተማሪዎቹን በቡድን የመከፋፈሉ ዓላማ በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ያለውን የጉዳይ ጥናት በቡድን እንዲወያዩበት ለማድረግ ታስቦ ነው። በመቀጠልም ተማሪዎቹ የተወያዩበትን ሃሳብ በቡድን እንዲቀያየሩ ጊዜ ስጧቸው። በተጨማሪም ተማሪዎቹ ሃሳብ በሚቀያየሩበት ወቅት የተቸገሩበት ጉድይ ካለ አግዟቸው። በመጨረሻም የተማሪዎቹን ግብረ መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማጠናከሪያ ሃሳብ ይስጡ።

ርህሩህነት የህብረተሰቡን ግንኙነት፣ አብሮ መኖርና ፍቅር ያጠናክራል። በዚህ መሰረት እኛ ወደ ሰው እንድንቀርብ ብቻ ሳይሆን ሰዎችም ወደ እኛ እንዲቀርቡ ለማድረግ ርህሩህነት ትልቅ ድርሻ አለው።

ክለሳ

ይህንን ክፍለ ትምህርት ተማሪዎችን በቃል ጥያቄ መገምገም ይችላሉ። የግምገማው ዋና ጥቅም ተማሪዎቹ ትምህርቱን ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅ ነው። ይህም የትምህርቱ ዓላማ ከግብ መድረሱን ለመገንዘብ የሚያግዝ ነው። በመማር ማስተማር ሂደት፣

- ተማሪዎቹ የትኛውን ትምህርት ወደዱት/መረጡት?
- ማንበብን፣መፃፍን ወይስ የቃል ጥያቄዎችን?
- ይህ ለምን እንድሆነ መግለፅ ትችላለህ?
- የተሰሩ የተግባር ክንውንን በተመልከተ የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ምን ያህል ነበር?
- ተማሪዎቹ በጥንድ፣በቡድን የተከናወኑ ስራዎችን ምን ያህል አብረው ሰርተዋል?
- በትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ የሰለቹበት ነጥብ/ጉዳይ አለ?

በተጨማሪም

ለማስታወስ ያህል ርህሩህነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎቹን ጠይቋቸው። ተማሪዎቹ የርህሩህነትን ጥቅም እንዲያስታውሱ የተለያ ጥያቄዎችን ጠይቁ።ተማሪዎቹ የተግባር ክንውን ሲሰሩ በመከታታል ብቃታቸውን መዝግቡ። የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎና ሙከራ በመገምገም ግብረ መልስ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ።

**4. ለጋስነት**

ከመልካምነት መርሆዎች ውስጥ አራተኛው ለጋስነት ነው። በመጀመሪያ ተማሪዎቹ ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን ስለ ርህሩህነትና አስፈላጊነቱ በማስታወስ ወደ ዕለቱ ትምህርት ርዕስ መሻገር አስፈላጊ ነው።

**ቁልፍና አነቃቂ ጥያቄዎች**

**ለጋስነትን እንዴት ትገልፃለህ/ሽ?**

ተማሪዎቹ ከላይ የተጠቀሱትን የማነቃቂያ ጥያቄዎች እንዲወያዩባቸው አድርጉ። የተማሪዎችን የሙከራ መልስ በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ለተማሪዎቹ የመነሻ ሃሳብ ሰንዝሩላቸው።

**በክፍለ ትምህርቱ የሚሰሩ ተግባራት፣ የቡድን ውይይትና የተግባር ክንውን**

ለዕለቱ ክፍለ ትምህርት እንዲመች የክፍል ተማሪዎቹን በቡድን በቡድን እንዲከፋፈሉ አድርጉ።የክፍል ተማሪዎቹን በቡድን የመከፋፈል ዓላማው በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ያለውን ሃሳብ እንዲወያዩበት ታስቦ ነው። በመቀጠልም ተማሪዎቹ ሃሳብ

እንዲቀያየሩ ጊዜ ስጧቸው። ተማሪዎቹ ሃሳብ በሚቀያየሩበት ወቅት የተቸገሩበት ጉድይ ካለ አግዟቸው።በመጨረሻም የተማሪዎቹን ግብረ መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማጠናከሪያ ይስጡ።

ለጋስነትን በተመለከተ ወሳኝ የሆኑ ቃላትን በሰሌዳው ላይ በመፃፍ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በተግባር ክንውን እንዲያሳዩ ዕድል ስጧቸው።የተማሪዎቹ የቡድን ክንውን ለጋሰነትን በተግባር እንዲተረጉሙ ለማገዝ ነው። በተጨማሪም በዕረፍት ጊዜያቸው ሁሉም ተማሪዎች የተግባር ክንውን እንዲሰሩ ፍቀዱላቸው።ተማሪዎቹ የተግባር ክንውኑን በሚሰሩበት ገዜ ያሳዩትን ብቃትና ልምዳቸውን መዝግቡ። በዚህ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የተግባር ክንውኑ የተፈለገበት ዋና ዓላማው ተማሪዎቹ ለጋስነትን በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ በተግባር እንዲለማመዱ ለማገዝ ነው።

**ክለሳ**

ይህንን ክፍለ ትምህርት ተማሪዎችን በቃል ጥያቄ ወይም እንደ ሌላው ክፍለ ትምህርት ሁሉ የቡድን ስራ በመስጠት መገምገም ይቻላሉ።የግምገማ ጥያቄዎቹ ዓላማ የዕለቱ ትምህርት ከግብ መድረሱን ለመገምገምና ተማሪዎቹ ትምህርቱን ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅ ነው።

- ተማሪዎቹ የትኛውን ትምህርት ወደዱት/መረጡት?
- ማንበብን፣መፃፍን ወይስ የቃል ጥያቄዎችን?
- ይህ ለምን እንድሆነ መግለፅ ትችላለህ?
- የተሰሩ የተግባር ክንውንን በተመልከተ የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ምን ያህል ነበር?
- ተማሪዎቹ በጥንድ፣በቡድን የተከናወኑ ስራዎችን ምን ያህል አብረው ሰርተዋል?
- በትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ የሰለቹበት ነጥብ/ጉዳይ አለ?

**በተጨማሪም**

ለጋስነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎቹን ጠይቋቸው። ተማሪዎቹ የለግስነትን አስፈላጊነት እንዲያስታውሱ የተለያዩ ጥያቄዎችን ጠይቁ።ተማሪዎቹ የተግባር ክንውኑን ሲሰሩ በመከታታል ብቃታቸውን መዝግቡ። የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎና ሙከራ በመገምገም ግብረ መልስ በመስጠት የክፍለ ትምህርቱን ማጠቃለያ ስጡ።

## 5. ፍትሃዊነት

ከመልካምነት መርሆዎች አምስተኛው ፍትሃዊነት ሲሆን የዚህ ክፍለ ትምህርት ዓላማም ተማሪዎቹ የፍትሃዊነት መርሆዎችን እንዲገነዘቡ ለማገዝ ነው። ይህ ክፍለ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የለጋስነተን ፅንሰ ሃሳብና አስፈላጊነት ተማሪዎቹን አስታውሷቸው። በመቀጠል የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎቹ በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ አድርጉ።

**ቁልፍ ቃላትና የማነቃቂያ ጥያቄዎች፣**

**ፍትሃዊነት ማለት ምን ማለት ነው?**

**አንድን ጉዳይ ፍትሃዊ ነው ወይም አይደለም የምንለው ምን ሁኔታ ሲከሰት ነው?**

**በክፍለ ትምህርቱ የሚሰሩ ተግባራት፣የቡድን ስራና የተግባር ክንውን**

ለክፍለ ትምህርቱ መማር ማስተማር እንዲመች የክፍል ተማሪዎቹን በቡድን በቡድን ይከፋፈሉ።ተማሪዎቹን በቡድን የመከፋፈሉ ዓላማ በቡድን ስለ ፍትሃዊነት እንዲወያዩበት ታስቦ ነው።በመቀጠልም ተማሪዎቹ ሃሳብ እንዲቀያየሩ ግዜ ስጧቸው። ተማሪዎቹ ሃሳብ በሚቀያየሩበት ወቅት የተቸገሩበት ጉድይ ካለ አግዟቸው። በመጨረሻም የተማሪዎቹን ግብረ መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማጠናከሪያ ይስጡ።

አንድ ተማሪ በድብቅ ወንጀል ሰርቶ የትምህርት ቤት ጓደኞቹ ውሳኔ ሲሰጡበት አይተህ ታውቃለህ? ፈተና መኮረጅ፣መስረቅ፣በትምህርት ወቅት መምህሩን አለመከታተል፣ የትምህርት ቤት ንብረትን መስረቅ የመሳሰሉት ተግባራት ከወንጀል ድርጊት ውስጥ የሚመደቡ ናቸው። ይሁን እንጂ ለእያንዳንዱ ወንጀል የራሱ የሆነ ቅጣት አለው።

ይህም ማለት ወንጀሎች ሁሉ ወንጀል ቢሆኑም አንድ ወንጀል በድርጊቱ ከሌላው ወንጀል ሊበልጥ ወይም ሊያንስ እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ተማሪዎቹ አንድ ወንጀል ተፈፀመ ብለው ገመቱ ወይም አሰቡ እንበል። ለዚህ ወንጀል ተገቢ ቅጣት ሊሆን ይችላል በሚለው ሃሳብ ላይ ግን የተለያየ አቋም በመያዝ እንዲከራከሩበት ያድርጉና የተማሪዎቹን ሙከራ በሰሌዳው ላይ ፃፏቸው። ይህ የተግባር ክንውን የተማሪዎቹን ምክንያት የማቅረብ ችሎታ ለማዳበርና ፍትሃዊነት በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ አስፈላጊ

መሆኑን ለማስገንዘብ ነው። በመቀጠልም ከፍርድ ቤት አንድ ባለሞያ በመጋበዝ የፍርድ አሰጣጥ ሂደትን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያብራሩ አድርጉ።

**ክለሳ**

የቃል ጥያቄና የክፍል ስራ በመስጠት ይህንን ክፍለ ትምህርት መገምገም ይችላሉ። የግምገማ ጥያቄዎቹ ዓላማ የዕለቱ ትምህርት ከግብ መድረሱን ለማረጋገጥ ነው። የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ምን ይመስላል? አብሮ ለማስራት ያላቸው ፍላጎትስ? በተግባር ክንውንስ ተማሪዎቹ የትኛውን ወደዱት፣ተማሪዎቹ የትኛውን ትምህርት ወደዱት/መረጡት?፣

ማንበብን፣መፃፍን ወይስ የቃል ጥያቄዎችን፣ ይህ ለምን እንደሆንነ መግለፅ ትችላለህ? የተሰሩ ተግባራትን በተመልከተ የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ምን ያህል ነበረ? ተማሪዎቹ በጥንድ፣በቡድን የተከናወኑ ስራዎችን ምን ያህል አብረው ሰርተዋል። በትምህርቱ በክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ የሰለቹበት ነጥብ/ጉዳይ አለ?

**በተጨማሪም**

ተማሪዎቹ እንዲያስታውሱ ፍትሃዊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ጥያቄ ይጠይቁ። ተማሪዎቹ የፍታሃዊነትን አስፈላጊነት እንዲያስታውሱ የተለያዩ ጥያቄዎችን ጠይቁ። ተማሪዎቹ የተግባር ክንውን ሲሰሩ በመከታታል ብቃታቸውን መዝግቡ። የእያንዳንዱ ተማሪ ተሳትፎና ሙከራ በመገምገም ግብረ ምልስ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ያጠቃሉ።

**6.አስተዋይነት**

ከመልካምነት መርሆዎች ውስጥ ስድስተኛው አስተዋይነት ነው። ይህም ማለት አስተዋይነት ከመልካምና ስነ ምግባር ባህሪያት ውስጥ የሚመደብ መሆኑን ያሳያል። ተማሪዎቹን ያለፈውን ትምህርት ካስታወሷቸው በኋላ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በሰሌዳው ላይ ፃፉና ተማሪዎቹ በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ አድርጉ።

**ቁልፍ ቃላትና የማነቃቂያ ጥያቄዎች፣**

አስተዋይነት ማለት ምን ማለት ነው? ለማስታወስ እንዲመችዎት የተማሪዎቹን የሙከራ መልስ በሰሌዳው ላይ ፃፉ?

አስተዋይነት ማለት ለአንድ ውሳኔ አለመቸኮል መልሶ መላልሶ ማሰብ ጥሩ ስነ ምግባርና መልካም ውሳኔ የመወሰን ችሎታን የሚያመለክት ነው። ይህም ማለት በኋላ የማንፀጸትበት ውሳኔ መወሰን መቻል ደግሞ የአስተዋይ ሰዎች መገለጫ ባህሪይ ነው።

**በዚህ ክፍለ ትምህርት የሚሰሩ ተግባራት፣ የቡድን ስራና የተግባር ክንውን**

ለክፍለ ትምህርቱ እንዲመች የክፍል ተማሪዎችን በተለያየ ቡድን ይከፋፍሉ።ተማሪዎቹን በቡድን የመከፋፈሉ ዓላማ በአስተዋይነትና አስፈላጊነቱ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ታስቦ ነው። በውይይት ወቅት ተማሪዎቹ አልፎ አልፎ ሃሳባቸውን እንዲቀያየሩ ፍቀዱላቸው። ተማሪዎቹ ሃሳብ በሚቀያየሩበት ወቅት የተቸገሩበት ጉድይ ካለ አግዟቸው። በመጨረሻም የተማሪዎቹን ግብረ መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማጠናከሪያ ሃሳብ ይስጡ።

ተማሪዎቹ የተግባር ክንውኑን በሚሰሩበት ጊዜ አስተዋይ መሆናቸውን ያሳዩት ብስለት አለ? ያላቸውን ብስለት በተግባር አሳይተዋል? በወረቀት ላይ አስተዋይነትን የሚገልፅ ሃሳብ ፃፉና ተማሪዎቹ ይህንን ሃሳብ አስመስለው በተግባር እንዲተውኑ አድርጉ። የተግባር ክንውኑን በሚከውኑበት ወቅት የተሰማቸውን ስሜት እንዲገልፁ አድርጉ። ተማሪዎቹ አስመስለው እንዲከውኑ የማድረጉ ዋና ዓላማ በህይወት ሂደት አስተዋይ ውሳኔ ለመወሰን እንዲረዳቸውና አስተዋይነት ውሳኔን እንዲለማመዱ ለማበረታታት ነው።

## ይዘት3. መልካምነት በተግባር ሲገለፅ

በዚህ ርዕስ ውስጥ ከተማሪው የሚጠበቁ ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች፡

ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- የመልካም ህብረተሰብ መገለጫ ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፡፡

| | ጉዳይ | የትምህርት ቁሳቁስና የሚሰሩ ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህርትመርጃ ቁሳቁስ | ጥቁር ሰሌዳ፣ቻርት፣የተማሪው መጽሐፍ፣እስክሪብቶና ወረቀት |
| 2 | የመማር ማስተማር ዘዴ | የቃል ጥያቄ፣ የቡድን ስራና የተግባር ክንውን |
| 3 | አባሪ መፃሕፍት | መጸሃፍት፣ በመልካምነት ላይ የተፃፉና ተያያዥነት ያላቸው አንቀፆችና የተለያዩ ፁሁፎች፣ |

ይህ ክፍለ ትምህርት በመልካም ህብረተሰብ ግንባታ ላይ ያተኩራል። በመጀመሪያ ካለፈው ትምህርት የአስተዋይነትን ፅንሰ ሃሳብ፣አስፈላጊነትና ጥቅም እንዲያስታውሱ ጠይቋቸው። በመቀጠል የዕለቱን ክፍለ ትምህርት ርዕስ በሰሌዳ ላይ ይፃፉና ተማሪዎቹ በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ አድርጉ።

**ቁልፍና የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- ስለ መልካምነት ምን ታውቃለህ/ሽ?
- የመልካም ህብረተሰብ መገለጫ ባህሪያትን አብራራ/ሪ?
- ፍትሃዊ ግብር ማለት ምን ማለት ነው?

ከላይ የተጠቀሱ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን በተመለከተ ተማሪዎቹ የተወሰነ ልምድ ሊኖራቸው ስለሚችል እንዲመልሱ በማድረግ ያላቸውን ልምድና መልስ በማቀናጀት በሰሌዳ ላይ ይፃፉ።

**በክፍለ ትምህርቱ የሚሰሩ ተግባራት፣የቡድን ስራና የተግባር ክንውን**

የክፍል ተማሪዎችን ለክፍለ ትምህርቱ በሚያመች ሁኔታ በተለያየ ቡድን ከፋፍሏቸው። ተማሪዎቹን በቡድን የመከፋፈሉ ዋና ዓላማ ተማሪዎቹ የሰላምን አስፈላጊነት በቡድን እንዲወያዩ ታስቦ ነው። ይህም ማለት የሰላምን አስፈላጊነት፣የህብረተሰቡን በሰላም የመኖር ዕሴት፣በመልካም ህብረተስብ ግንባታ ውስጥ የሰላምን ጥቅም ተማሪዎቹ እንዲያስቡና እንዲወያዩ ለማድረግ ነው።ተማሪዎቹ ሃሳብ በሚለዋወጡበት ጊዜ የገጠማቸው ችግር ካለ አግዟቸው። በመቀጠልም ተማሪዎቹ ሃሳብ እንዲቀያየሩ ጊዜ ስጧቸው። ለተወሰነ ግዜ ከተወያዩ በኋላ በክፍል ውስጥ ሃሳባቸውን እንዲያብራሩ አድርጉ። በመጨረሻም የተማሪዎቹን ግብረ መልስ በማቀናበር በሰሌዳ ላይ በመፃፍ የማጠቃለያ ሃሳብ ይስጡ።

**ፍትሃዊ የሆነ ግብር የመክፈል ጥቅም**፡-ፍትሃዊ ግብር መክፈል ማለት ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ አንፃር የተመጣጠነ ግብር መክፈል መቻል ማለት ነው። ይህም ማለት፣

- ብዙ ገቢ ያላችው ሰዎች ብዙ ግብር መክፈል ሲጠበቅባቸው ትንሽ ገቢ ያላቸው ሰዎች ደግሞ ትንሽ ግብር መክፈል ይጠበቅባቸዋል። ይህም ማለትደግሞ ዜጎች በገቢያቸው መጠን ግብር መክፈል አለባቸው ማለት ነው። በዚህ መሰረት ከዜጎች የሚሰበሰበው ገንዘብ ለመንገድ ሰራ፣ለትምህርት ቤት፣ጤና ጣቢያ፣ለማህበረሰቡ አገልግሎት የሚውል ይሆናል።

- በሌላ በኩል ብዙ ገቢ ያላቸው ብዙ ግብር ሲከፍሉ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ሰዎች ላይ ጫናው ይቀንሳል ማለት ነው፡፡
- የሚሰበሰበው ገንዘብ የመንግስትን ገቢ ያሳድጋል፡፡

እንደ ሌላው ክፍለ ትምህርት ሁሉ ለዚህም ክፍለ ትምህርት የቃል ጥያቄና የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎችን መገምገም ይችላሉ።እነዚህ የግምገማ ጥያቄዎች ደግሞ ትምህርቱ ምን ያህል ከታሰበው ዓላማ እንደደረሰ ለማወቅ ይጠቅማል።

**ክለሳ**

የቃል ጥያቄና የክፍል ስራ በመስጠት ይህንን ትምህርት መገምገም ይችላሉ።የግምገማ ጥያቄዎቹ የትምህርቱን ዓላማ ከግብ መድረሱን ለመገምገም ያግዛል። የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ክህሎት ምን ይመስላል? አብሮ ለማስራት ያላቸው ፍላጎትስ? በተግባር ክንውኑስ ተማሪዎቹ የትኛውን ወደዱት?

- ተማሪዎቹ የትኛውን ትምህርት ወደዱት/መረጡት?፣
- ማንበብን፣መፃፍን ወይስ የቃል ጥያቄዎችን?
- ይህ ለምን እንደሆነ መግለፅ ትችላለህ/ሽ?
- የተሰሩ ተግባራትን በተመልከተ የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ብቃት ምን ያህል ነበረ?
- ተማሪዎቹ በግል፣ በጥንድ፣በቡድን የተከናወኑ ስራዎችን ምን ያህል አብረው ሰርተዋል
- በትምህርት በክፍለ ግዜ ተማሪዎቹ የሰለቹብት ነጥብ/ጉዳይ አለ?

**በተጨማሪም**

መልካም ህብረተሰብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎቹን ጠይቋቸው። ተማሪዎቹ የመልካም ህብረተሰብን አስፈላጊነት እንዲያስታውሱ የተለያዩ ጥያቄዎችን ጠይቋ። ተማሪዎቹ የተግባር ክንውን ሲሰሩ በመከታታል ክህሎታቸውን መዝግቡ። የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎና ሙከራ በመገምገም ግብረ መልስ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለያ ይስጡ።

# ይዘት4. የመልካምነት አስፈላጊነት

**በዚህ ርዕስ ውስጥ ከተማሪው የሚጠበቁ ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች**

**ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ**

- **የመልካምነትን አስፈላጊነት ያብራራሉ፤**
- **የመልካምነትን ጥቅምና ውጤት ይዘረዝራሉ፡፡**

| | ጉዳይ | የመማሪያ ቁሳቁስና የሚሰሩ ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ | ጥቁር ሰሌዳ፣ቻርት፣የተማሪው መፀሃፍ፣እስክሪብቶና ወረቀት |
| 2 | የመማር ማስተማር ዘዴ | የቃል ጥያቄ፣ የቡድን ስራና የተግባር ክንውን |
| 3 | አባሪ መፃሕፍት | መጻሕፍት፣ በመልካምነት ላይ የተፃፉና ተያያዥነት ያላቸው አንቀፆች፣ የተለያዩ ጽሁፎች፣ |

**መግቢያ**

ይህ ክፍለ ትምህርት በመልካምነት ባህሪ በይበልጥ ደግሞ በመልካምነት አስፈላጊነት ላይ ያተኩራል። በባለፈው ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ ስለ መልካምነት፣መልካም ህብረተሰብ፣ የመልካም ህብረተሰብ አስፈላጊነት የመልካም ህብረተሰብ መገለጫ ባህሪያትን ተምረዋል። በመቀጠልም የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በሰሌዳ ላይ ይፃፉና ተማሪዎቹ በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ አድርጉ።

**ቁልፍ ቃላትና የማነቃቂያ ጥያቄዎች፣**

ስለ መልካምነት አስፈላጊነት ምን ታውቃላችሁ?

መልካምነት ምን አይነት ጥቅሞች አሉት?

ለዕለቱ ክፍለ ትምህርት እንዲመችዎት ተማሪዎችን በተለያየ ቡድን ከፋፍሏቸው። ተማሪዎቹን በቡድን የመከፋፈሉ ዓላማ የመልካምነትን አስፈላጊነት እንዲያስቡና እንዲወያዩበት ለማድረግ ነው። ተማሪዎቹ ሃሳብ በሚለዋወጡበት ጊዜ የተቸገሩበት ጉዳይ

ካለ አግዟቸው። ለተወሰነ ጊዜ ከተወያዩ በኋላ በክፍል ውስጥ የተወያዩበትን ሃሳብ እንዲያብራሩ አድርጉ። በመጨረሻም የተማሪዎቹን ግብረ መልስ በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማጠቃለያ መስጠት ይችላሉ።

**በክፍለ ትምህርቱ የሚሰሩ ተግባራት፣የቡድን ስራ**

የክፍል ተማሪዎችን ለመከታተል በሚያመችዎት መልኩ ተማሪዎችን በተለያየ ቡድን ከፋፍሏቸው። ተማሪዎቹን በቡድን የመከፋፈሉ ዋና ዓላማ የመልካምነትን አስፈላጊነት በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ እንዴት ሊተገበር እንደሚችል እንዲወያዩበት ለማድረግ ታስቦ ነው። ተማሪዎቹ በሚወያዩበት ወቅት አልፎ አልፎ ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡ ዕድል ስጧቸው።ተማሪዎቹ ሃሳብ በሚቀያየሩበት ወቅት የተቸገሩበት ጉድይ ካለ አግዟቸው። በመጨረሻም የተማሪዎቹን ግብረ መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማብራሪያ በመስጠት ማጠቃለል ይችላሉ።

**ክለሳ**

የተማሪዎችን ሙከራ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ መገምገም ይችላሉ። በተጨማሪም እንደሌላው ትምህርት ሁሉ የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎችን መገምገም ይችላሉ። የግምገማ ጥያቄዎቹ ዓላማ ትምህርቱ ከታሰበው ግብ መድረሱን ለማወቅ ነው።እንዲሁም ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን የቤት ስራ መስራታቸውን በማየት መገምገም ይችላሉ። የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ምን ይመስላል? አብሮ ለማስራት ያላቸው ፍላጎት? በተግባር ክንውንስ? ተማሪዎቹ የትኛውን ወደዱት? ተማሪዎቹ የትኛውን ትምህርት ወደዱት/መረጡት? ማንበብን፣መፃፍን ወይስ የቃል ጥያቄዎችን? ይህ ለምን እንደሆነ መግለፅ ትችላለህ? የተሰሩ ተግባራትን በተመለከተ የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ምን ያህል ነበረ? ተማሪዎቹ በግል፣ በጥንድ፣በቡድን የተከናወኑ ስራዎችን ምን ያህል አብረው ሰርተዋል? በትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ የሰለቹበት ነጥብ/ጉዳይ አለ?

**በተጨማሪም፣**

ያለፈውን ትምህርት እንዲያስታውሱ ስለ መልካምነት ጥቅምና አስፈላጊነት ጠይቋቸው። እያንዳንዱ ተማሪ የተሰጠውን ተግባር በደንብ መከወኑን በመከታተል ማጠቃለያ በመስጠት የዕለቱን ክፍለ ትምህርት መቋጨት ይችላሉ።

# ይዘት 5. መልካምነት በተግባር ሲገለፅ/ በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ

በዚህ ርዕስ ውስጥ ከተማሪው የሚጠበቁ ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች

ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- መልካምነት በዕለት ተዕለት ህይወት በተግባር እንዴት እንደሚገልፅ ይዘረዝራሉ፣

| | ጉዳይ | የመማሪያ ቁሳቁስና የሚሰሩ ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ | ጥቁር ሰሌዳ፣ቻርት፣የተማሪው መጽሃፍ፣እስክሪብቶና ወረቀት |
| 2 | የመማር ማስተማር ዘዴ | የቃል ጥያቄ፣ የቡድን ስራና የተግባር ክንውን |
| 3 | አባሪ መፃሕፍት | የተለያዩ መጻሕፍት፣በመልካምነት ላይ የተፃፉና ተያያዥነት ያላቸው አንቀፆች ፣የተለያዩ ጽሁፎች፣ http://www.shivajicollege.ac.in |

ይህ ክፍለ ትምህርት በመልካምነት ባህሪይ በይበልጥ ደግሞ በመልካም ተግባራት ላይ ያተኩራል። በባለፈው ክፍለ ጊዜ ስለ መልካምነት፣መልካም ህብረተሰብ፣የመልካም ህብረተሰብ አስፈላጊነት፣ የመልካም ህብረተሰብ መገለጫ ባህሪያትን ተምረዋል። በዚህ ክፍለ ጊዜ ደግሞ መልካምነት በተግባር እንዴት እንደሚተገበር ይማራሉ። በዚሁ መሰረት የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በሰሌዳ ላይ ፃፉና ተማሪዎቹ በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ አድርጉ።

**ቁልፍ ቃላትና የማነቃቂያ ጥያቄዎች፣**

**መልካምነት በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ አስፈላጊ ነው ብለህ/ሽ ታምናለህ/ሽ?**

ለክፍለ ትምህርቱ በሚያመች መልኩ የክፍል ተማሪዎችን በቡድን እንዲደራጁ አድርጉ። ተማሪዎቹን በቡድን የማደራጀት ዋና አላማ መልካምነት እንዴት በተግባር እንደሚገለፅ እንዲያስቡና እንዲወያዩበት ለማድረግ ታስቦ ነው። ተማሪዎቹ ሃሳብ በሚለዋወጡበት ጊዜ የተቸገሩበት ጉዳይ ካለ አግዟቸው። ለተወሰነ ጊዜ ከተወያዩ በኋላ በክፍል ውስጥ ሃሳባቸውን እንዲያብራሩ አድርጉ። በመጨረሻም የተማሪዎቹን ግብረ መልስ በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማጠቃለያ ይስጡ።

**በክፍል ትምህርቱ የሚሰሩ ተግባራት፣የወ/ሮ አበበች ጎበና ታሪክን መልሶ በተግባር መከወን**

በተማሪው የመማሪያ መጽሃፍ ውሰጥ የወ/ሮ አበበች ጎበና የህይወት ታሪክ እንደ ጥሩ ምሳሌ ቀርቧል። የሳቸው መልካም ተሳትፎ በህብረተሰቡ ውሰጥ ምን ያህል ለውጥ እንዳመጣ ተማሪዎቹ እንዲወያዩበት አድርጉ። ከዚያ በኋላ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ነጥብ በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎቹ በተግባር እንዲከውኑ በማድረግ ለተማሪዎቹ ግበረ መልስ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ።

**ክለሳ**

የተማሪዎችን ሙከራ የቃል ጥያቄ በመስጠት መገምገም ይችላሉ። በተጨማሪም እንደ ሌላው ትምህርት ሁሉ ይህንንም ትምህርት የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎችን መገምገም ይቻላል። የግምገማ ጥያቄዎቹ ዓላማ ትምህርቱ ከታሰበው ግብ መድረሱ ለማወቅ ነው። የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ምን ይመስላል? አብሮ ለማስራት ያላቸው ፍላጎትስ? በተግባር ክንውንስ? ተማሪዎቹ የትኛውን ትምህርት ወደዱት/መረጡት?፣በይበልጥ ማንበብን፣መፃፍን ወይስ የቃል ጥያቄዎችን? ይህ ለምን እንደሆነ መግለፅ ትችላለህ/ሽ? የተግባር ክንውኑን በተመለከተ የተማሪዎቹ በራስ መተማመን ምን ያህል ነበር? ተማሪዎቹ በግል፣ በጥንድ፣በቡድን የተከናወኑ ስራዎችን ምን ያህል አብረው ሰርተዋል? በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ የሰለቹበት ነጥብ/ጉዳይ አለ?

**በተጨማሪም**

ተማሪዎቹ ያለፈውንትምህርት እንዲያስታውሱ ስለ መልካምነት መገለጫ ባህሪያት ጠይቋቸው።በተጨማሪ መልካምነት በተግባር እንዴት እንደሚገልፅ እያንዳንዱን ተማሪ ጠይቁ? ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን ጥያቄና የተግባር ክንውን በደንብ መከወናቸውን በመከታተል ግብረ መልስና የማጠቃለያ ሃሳብ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለል ይችላሉ።

**የማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ**

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የእውነት/ሀሰት ጥያቄዎች | 1 | ሀሰት | 2 | እውነት | 3 | እውነት | 4 | ሀሰት | | |
| የምርጫ ጥያቄዎች | 1 | B | 2 | C | 3 | B | 4 | D | | |

# ምዕራፍ 2

## መንግስት እና የመንግስት አስተዳደር

**ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ብዛት ……………………16**

### መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ሥር ተማሪዎች ስለ መንግስት አወቃቀር፣ ስለ መንግስት ስርዓት እና በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካከል ያሉትን ግንኙነቶች እና ልዩነቶች ይማራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያን የመንግስት ሥርዓቶች በሰፊው የሚማሩበት ክፍል ነው፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡-** መንግስት፣ የመንግስት አስተዳደር፣ አሃዳዊ፣ ፌዴራላዊ፣ ፕሬዝዳንታዊ፣ ፓርላሜንታዊ

| የመማር ውጤቶች | የትምህርት ይዘቶች |
|---|---|
| ✎ የተለያዩ የመንግስት መዋቅሮችን ይለያሉ፤<br>✎ የተለያዩ የመንግስት ስርዓቶችን ይገልፃሉ፤<br>✎ በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካከል ያለውን ግንኙነት እና ልዩነት ይለያሉ፤<br>✎ የኢትዮጵያን የመንግስት ሥርዓት ይገነዘባሉ፤<br>✎ የኢትዮጵያ የመንግሰት አስተዳደር ጥንካሬዎች እና ውስንነቶችን ይገልፃሉ፡፡ | 2.1. የመንግስት አወቃቀር<br>2.2. የመንግስት ስርዓቶች<br>2.3. በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካከል ያለው ግንኙነት እና ልዩነት<br>2.4.የኢትዮጵያ የመንግስት ሥርዓት<br>2.4.1. የኢትዮጵያ የመንግሰት አስተዳደር ጥንካሬዎች እና ውስንነቶች |

# ይዘት 1. የመንግስት አወቃቀር

ተማሪ ሊጎናፀፉ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፡-

- የመንግስት አወቃቀር ፅንሰ ሀሳቦችን ይገልፃሉ፤
- የመንግስት አወቃቀር አይነቶችን ይለያሉ፤
- የመንግስት አወቃቀር ባህራትን ይዘረዝራሉ፤
- የተለያዩ የመንግሰት አስተዳደር ጥንካሬዎች እና ውስንነቶችን ይለያሉ፡፡

## ማብራሪያ

በዚህ ርዕስ ላይ ተማሪዎች ስለ መንግስት አወቃቀር ይማራሉ፡፡ የመንግስት አወቃቀር ጽንሰ ሀሳብ ሥልጣን በሕገመንግሥቱ መሰርት ወደ ዝቅተኛ የአስተዳደር አካላት መከፋፈል ወይም በማዕከላዊ መንግሥት መያዙን የሚገልፅ ነው።ለምሳሌ በኢትዮጵያ የክልል መንግስታት ስልጣን እና ተግባር በህገመንግስታዊ መንገድ የተሰጠ ሲሆን በኬንያ ግን ሁሉንም ስልጣን የፌዴራል መንግስት ይቆጣጠራል። በተለያዩ ሀገራት የተለያዩ የመንግስት መዋቅሮች ሊኖሩ ይችላሉ ይሁን እንጂ ዋና ዋና የመንግሰት መዋቅሮች የሚባሉት ሶስት ናቸው። እነሱም፡-አሃዳዊ፣ፌዴራላዊ እና ኮንፌዴራላዊ ናቸው።የፌደራላዊ እና አሃዳዊ ስርዓቶች በመላው አለም በብዛት የተለመዱ ሲሆኑ የኮንፌዴራላዊ ስርዓት ግን ብዙም የተለመደ አይደለም።

## የመማር ማስተማር ሂደት

| ተ.ቁ | ማዕቀፍ | ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህረት መርጃ መሳሪያዎች | ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ፣ እርሳሶች፣ ሥዕሎች፣ እና የገበታ ወረቀት |
| 2 | የማስተማር ስልቶች | የማነቃቂያ ጥያቄ፣ መግቢያ እና ማብራሪያ ፣ የግል ስራዎች, የቡድን ውይይት እና አቀራረብ |
| 3 | የማጣቀሻ ቁሳቁስ | በመንግስት አወቃቀር ላይ የተፃፉ መጣጥፎች እና መጽሔቶች http://www.shivajicollege.ac.in |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | ቅድመ ዝግጅት | ✍ የርዕስ እቅድን ማዘጋጀት እና በክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት ማቀናጀት<br>✍ የተለያዩ የማጣቀሻ መጻሕፍትን በማንበብ በደንብ መዘጋጀትና የትምህረት የመርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት |
| 5 | የርዕስ<br>አቀራረብ | የትምህርቱ መግቢያ<br>✍ የመማር ማስተማር ሂደት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው፡፡<br>✍ የዕለቱን ርዕስ ቀለል ባለ አቀራረብ እና በጥያቄ ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡ |
| | | የትምህርቱ አካል<br>✍ በመንግስት መዋቅር ላይ እውቀት መፍጠር<br>✍ ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎች በማስታዋሻ ደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ ሰፊ ማብራሪያዎችን ያድርጉ |
| | | ምዘና እና ግምገማ<br>✍ የትምህርቱን ማጠቃለያ ማድረግ፣ የክትትል ስራዎችን እና ጥያቄዎችን በቃል ማቅረብ፣ አስፈላጊ ከሆነ የክፍል ፈተና መስጠት ይችላሉ፡፡<br>✍ እነዚህም የግምገማ ጥያቄዎች የትምህርቱ ዓላማዎች ምን ያህል እንደተሳኩ ለመገምገም ይረዱዎታል፡፡<br>☞ **ግምገማ**<br>✍ በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪዎችዎ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የትምህርቱን አስፈላጊ ዕንሰ ሀሳቦች መረዳታቸውን ያረጋግጡ፡፡<br>☞ **ክትትል**<br>✍ ተማሪዎቹ የዕለቱን ርዕስ መገንዘባቸውን ለማወቅ በተናጠል የተለያዩ ጥያቄዎች በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ ። |

 የመንግስት መዋቅር ምንድን ነው?

የመንግስት አወቃቀር ማለት ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ ወደ ዝቅተኛ የአስተዳደር አካላት መሰጠቱ ወይም በማዕከላዊ መንግሥት መያዙን የሚያመለክት ነው። ዓለም በሦስት የመንግስት መዋቅሮች የተከፋፈለች ናት፡፡ እነሱም፡- አሃዳዊ፣ ፌዴራላዊ እና ኮንፌዴራላዊ ናቸው። ከእነዚህም መካከል የፌደራላዊ እና አሃዳዊ መዋቅሮች በመላው አለም በብዛት የተለመዱ ሲሆኑ የኮንፌዴራላዊ መዋቅር ግን ብዙም የተለመደ አይደለም።

## ይዘት 2. አሃዳዊ የመንግስት መዋቅር

ተማሪ ሊጎናፀፍ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፡-

- አሃዳዊ የመንግስት መዋቅርን ይግልፃሉ፤
- የአሃዳዊ መንግስት መዋቅር ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፡፡

### ማብራሪያ

በዚህ ርዕስ ሥር ተማሪዎች ስለ አሃዳዊ የመንግስት አወቃቀር ይማራሉ፡፡እንዲሁም የአሃዳዊ የመንግስት አወቃቀር ባህሪያትን፣ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖቹን ለይተው ይማራሉ፡፡ አሃዳዊ መንግስት ማለት ሥልጣን በማዕከላዊነት የሚታወቅ ሲሆን ማዕከላዊ መንግሥት ሁሉንም የመንግሥት አካላት የሚቆጣጠርበት የመንግሥት መዋቅር ዓይነት ነው።

### የመማር ማስተማር ሂደት

| ተ.ቁ | ማዕቀፍ | ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህረት መርጃ መሳሪያዎች | ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ፣ እርሳሶች፣ ሥዕሎች፣ እና ሠንጠረዥ |
| 2 | የማስተማር ስልቶች | የማነቃቂያ ጥያቄ፣ መግቢያ እና ማብራሪያ ፣ የግል ስራዎች፣የቡድን ውይይት እና አቀራረብ |
| 3 | የማጣቀሻ ቁሳቁስ | በአሃዳዊ የመንግስት አወቃቀር ላይ የተፃፉ መጣጥፎች እና መጽሔቶች፣ http://www.shivajicollege.ac.in |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | ቅድመ ዝግጅት | ✍ የርዕስ እቅድን ማዘጋጀት እና በክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት ማቀናጀት<br>✍ የተለያዩ የማጣቀሻ መጻሕፍት በማንበብ በደንብ መዘገጀትና የትምህረት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት |
| 5 | የርዕስ<br>አቀራረብ | የትምህርቱ መግቢያ<br>✍ የመማር ማስተማር ሂደት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው፡፡<br>✍ የዕለቱን ርዕስ ቀለል ባለ አቀራረብ እና በጥያቄ ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡<br>ለምሳሌ፡- አሃዳዊ የመንግስት መዋቅር ምንድንነው? |
| | | የትምህርቱ አካል<br>✍ በአሃዳዊ የመንግስት መዋቅር ላይ እውቀት መፍጠር<br>✍ ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎች በማስታዋሻ ደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ ሰፊ ማብራሪያዎችን ያድርጉ |
| | | ሚዘና እና ግምገማ<br>✍ የትምህርቱን ማጠቃለያ ማድረግ፣ የክትትል ስራዎችን እና ጥያቄዎችን በቃል ማቅረብ፣ አስፈላጊ ከሆነ የክፍል ፈተና መስጠት ይችላሉ፡፡<br>✍ እነዚህም የግምገማ ጥያቄዎች የትምህርቱ ዓላማዎች ምን ያህል እንደተሳኩ ለመገምገም ይረዱዎታል<br>☞ **ግምገማ**<br>✍ በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪዎችዎ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የትምህርቱን አስፈላጊ ፅንሰ ሀሳቦች መረዳታቸውን ያረጋግጡ<br>☞ **ክትትል**<br>✍ ተማሪዎቹ የዕለቱን ርዕስ መገንዘባቸውን ለማወቅ በተናጠል የተለያዩ ጥያቄዎች በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ ። |

## የተግባር 1 መልስ

ተማሪዎች የሚከተለውን ሠንጠረዥ ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ከገለበጡ በኋላ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩበትና ሠንጠረዡን እንዲሞሉ ያበረታቱ፡፡ በስተመጨረሻም የቡድኑ ተወካይ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡

| ተ.ቁ | ባህሪያት | ጥቅሞች | ድክመቶች |
|---|---|---|---|
| 1 | ሥልጣን ሙሉ በሙሉ በማዕከላዊ መንግስት መቆጣጠር | የአስተዳደር ወጥነት እንዲኖር ያደርጋል | ለብዝሃነት እውቅናን አይሰጥም |
| 2 | ማዕከሉ ያልተገደበ ሥልጣን ያለው እና በህጋዊ መንገድ በክልል ወይም በአከባቢ ግዛቶች ላይ የበላይ ነው። | በማዕከሉ እና በክልል መካከል ባለው የስልጣን ክፍፍል ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የስልጣን ግጭት ያስወግዳል። | ማህበረሰቡን በቅርበት ለማስተዳደር አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። |
| 3 | የንዑስ ክፍሎች የሕግ አውጪ አካላት ለማዕከሉ የሕግ አውጪ አካል ሪፖርት ያደርጋሉ። | የህዝብ አገልግሎት እና እኩል ተደራሽነትን ያቀላጥፋል | የስልጣን ክምችት በማዕከላዊ መንግስት እንዲኖር ያደርጋል |
| 4 | የክልል ንኡስ ክፍሎች ለማዕከሉ የበታች ናቸው እና ራሳቸውን ችለው መሥራት አይችሉም። | በሁሉም ክልሎች ተመሳሳይ አስተዳደር ለመስጠት ይረዳል | ራስን በራስ የማስተዳደር መብት አያበረታታም |

## ይዘት3. የፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር

ተማሪዎቸወ ሊጎናፃፉ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፡-

- የፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር ፅንሰ ሀሳብን ይገልፃሉ፤
- የፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፡፡

## ማብራሪያ

በዚህ ርዕስ ሥር ተማሪዎች የፌደራላዊ መንግስት አወቃቀር ፅንሰ ሀሳብ እና ባህሪያትን እንዲገልፁ ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም ተማሪዎች የፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር ጥቅሞች እና ጉዳቶችን መለየት አለባቸው፡፡ ፌዴራሊዝም ቢያንስ ሁለት የአስተዳደር እርከኖች ያሉት መንግስታዊ መዋቅር ሲሆን እነሱም ማዕከላዊ መንግስት እና የክልል መንግስታት ናቸው፡፡ የማዕከላዊው የመንግስት አገራቱን በሙሉ ያስተዳድራል። መከላከያ፣ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ የዜግነት፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ እና እንደ ወደቦች እና አየር ማረፊያዎች ፣ አገራዊ መሠረተ ልማቶች በፌዴራል መንግሥት ይተዳደራሉ። የክልል መንግስታትን ሥልጣንና ተግባር የሚመለከቱ ጉዳዮችም አሉ። እነርሱም፡-ራስን በራስ የማስተዳደር፣ የዴሞክራሲ ሥርዓትን መገንባት፣ የሕግ የበላይነትን የማስፋፋትና የማሳደግ ሥልጣን አላቸው። የፌዴራል ሕገ መንግሥትን መጠበቅ እና መከላከል የክልሉን ሕገ መንግሥት እና ሌሎች ሕጎችን ማውጣትና ማስከበር፣ እንዲሁም የክልል ፖሊስን ማስተዳደር እና ህዝባዊ ጸጥታን ማስከበር እና በመንግስት ውስጥ ሰላምን ማስጠበቅ የክልል መንግስታት ስልጣን ናቸው።

## የመማር ማስተማር ሂደት

| ተ.ቁ | ማዕቀፍ | ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህረት መርጃ መሳሪያዎች | ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ፣ እርሳሶች፣ ሥዕሎች፣ እና ሠንጠረዥ |
| 2 | የማስተማር ስልቶች | የማነቃቂያ ጥያቄ፣ መግቢያ እና ማብራሪያ ፣ የግል ስራዎች, የቡድን ውይይት እና አቀራረብ |
| 3 | የማጣቀሻ ቁሳቁስ | በፌዴራላዊ የመንግስት አወቃቀር ላይ የተፃፉ መጣጥፎች እና መጽሔቶች፣ http://www.shivajicollege.ac.in |
| 4 | ቅድመ ዝግጅት | ✍ የርዕስ እቅድን ማዘጋጀት እና በክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት ማቀናጀት<br>✍ የተለያዩ የማጣቀሻ መፅሐፍትን በማንበብ በደንብ መዘጋጀትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | የርዕስ አቀራረብ | የትምህርቱ መግቢያ<br>✍ የመማር ማስተማር ሂደት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው፡፡<br>✍ የዕለቱን ርዕስ ቀለል በለ አቀራረብ እና በጥያቄ ልጀምሩ ይችላሉ፡፡<br>ለምሳሌ፡- ፌዴራላዊ የመንግስት መዋቅር ምንድንነው? |
| | | የትምህርቱ አካል<br>✍ በፌዴራላዊ የመንግስት መዋቅር ላይ እውቀት መፍጠር<br>✍ ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎች በማስታዋሻ ደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ ሰፊ ማብራሪያዎችን ያድርጉ |
| | | ምዘና እና ግምገማ<br>✍ የትምህርቱን ማጠቃለያ ማድረግ፣ የክትትል ስራዎችን እና ጥያቄዎችን በቃል ማቅረብ፣ አስፈላጊ ከሆነ የክፍል ፈተና መስጠት ይችላሉ፡፡<br>✍ እነዚህም የግምገማ ጥያቄዎች የትምህርቱ ዓላማዎች ምን ያህል እንደተሳኩ ለመገምገም ይረዱዎታል፡፡<br>☞ **ግምገማ**<br>✍ በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪዎችዎ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የትምህርቱን አስፈላጊ ፅንሰ ሀሳቦች መረዳታቸውን ያረጋግጡ<br>☞ **ክትትል**<br>✍ ተማሪዎቹ የዕለቱን ርዕስ መገንዘባቸውን ለማወቅ በተናጠል የተለያዩ ጥያቄዎች በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ ። |

## የተግባር 2 መልስ

ተማሪዎችን በቡድን ከከፈሉ በኋላ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 51 እና 52 አንብበው የሚከተለውን ጥያቄ እንዲሰሩ አድርጓቸው፡፡ በስተመጨረሻም የቡድኑ ተወካይ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡

 በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 51 እና 52 ምንን ይገልፃሉ?

በፌዴራላዊ መዋቅር ውስጥ የማዕከላዊ እና የክልል መንግስታት ሥልጣን በህገ መንግስት የተከፋፈለ ነው፡፡ ህገ መንግስቱም የፌዴራል ግንኙነቱ በቋሚ የጎብረት ቃል ኪዳን በመሆን የሚያገለግል ነው፡፡ይህም ብዙውን ጊዜ ሥልጣን እንዴት እንደሚከፋፈል የሚገልጽ ሰነድ መሆኑ ነው፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51 ለምሳሌ የፌዴራል መንግሥት ሥልጣንና ተግባርን ይዘረዝራል። ከእነዚህም መካከል ገንዘብ ማሳተም፣ አለም አቀፍ ግንኙነት ማከናወን ፣ ዜግነት፣ የሀገር መከላከያ፣ ከአስተዳደር እና ድንበር ተሻጋሪ መሰረተ ልማቶች እና ሃብቶችን አጠቃቀም ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ስልጣኖች እንዳለው ያትታል።

በሌላ በኩል አንቀጽ 52 የክልል መንግስታትን ሥልጣንና ተግባር ይመለከታል። እነርሱም፡-ራስን በራስ የማስተዳደር፣ የዴሞክራሲ ሥርዓትን፣ የሕግ የበላይነትን የማስፈንና የማሳደግ ሥልጣን አላቸው። የፌዴራል ሕገ መንግሥትን መጠበቅ እና መከላከል የክልሉን ሕገ መንግሥት እና ሌሎች ሕጎችን ማውጣትና ማስከበር፣ እንዲሁም የክልል ፖሊስን ማስተዳደር እና ህዝባዊ ጸጥታን ማስከበር እና በመንግስት ውስጥ ሰላምን ማስጠበቅ በተጨማሪ የክልል መንግስታት ስልጣን ናቸው።

# ይዘት 4፡ ኮንፌዴራላዊ የመንግስት አወቃቀር

**ተማሪዎች ሊጎናፀፏዋቸው የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፡-**

- የኮንፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር ፅንሰ ሀሳብን ይገልፃሉ፤
- የኮንፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር ባህሪያትን ይለያሉ፡፡

**ማብራሪያ**

በዚህ የትምህርት ይዘት ሥር ተማሪዎች ስለ ኮንፌዴራላዊ የመንግስት አወቃቀር ይማራሉ፡፡ ኮንፌዴሬሽን የሚመሰረተው በሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑት ሀገራት መካከል ሲሆን ዋና ዋና ዓላማዎቹም ብዙውን ጊዜ የጋራ መከላከያን፣ የጋራ የፖስታ አገልግሎቶችን እና የመገናኛ መዋቅሮችን ፣ የንግድ ልምዶችን እና የባህል አንድነት መለኪያዎችን ያካትታሉ።

**የመማር ማስተማር ሂደት**

| ተ.ቁ | ማዕቀፍ | ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህረት መርጃ መሳሪያዎች | ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ፣ እርሳሶች፣ ሥዕሎች፣ እና ሠንጠረዥ |
| 2 | የማስተማር ስልቶች | የማነቃቂያ ጥያቄ፣ መግቢያ እና ማብራሪያ ፣ የግል ስራዎች, የቡድን ውይይት እና አቀራረብ |
| 3 | የማጣቀሻ ቁሳቁስ | በኮንፌዴራላዊ የመንግስት አወቃቀር ላይ የተፃፉ መጣጥፎች እና መጽሔቶች፣ http://www.shivajicollege.ac.in |
| 4 | ቅድመ ዝግጅት | - የርዕስ እቅድን ማዘጋጀት እና በክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት ማቀናጀት<br>- የተለያዩ የማጣቀሻ መፅሕፍት በማንበብ በደንብ መዘጋጀትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | የርዕስ<br>አቀራረብ | የትምህርቱ መግቢያ<br>✍ የመማር ማስተማር ሂደት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው፡፡<br>✍ የዕለቱን ርዕስ ቀለል ባለ አቀራረብ እና በጥያቄ ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡<br>ለምሳሌ፡- ኮንፌዴራላዊ የመንግስት መዋቅር ምንድንነው? |
| | | የትምህርቱ አካል<br>✍ በኮንፌዴራላዊ የመንግስት መዋቅር ላይ እውቀት መፍጠር<br>✍ ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎች በማስታዋሻ ደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ ሰፊ ማብራሪያዎችን ያድርጉ |
| | | ምዘና እና ግምገማ<br>✍ የትምህርቱን ማጠቃለያ ማድረግ፣ የክትትል ስራዎችን እና ጥያቄዎችን በቃል ማቅረብ፣ አስፈላጊ ከሆነ የክፍል ፈተና መስጠት ይችላሉ፡፡<br>✍ እነዚህም የግምገማ ጥያቄዎች የትምህርቱ ዓላማዎች ምን ያህል እንደተሳኩ ለመገምገም ይረዱዎታል<br>☞ **ግምገማ**<br>✍ በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪዎችዎ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የትምህርቱን አስፈላጊ ፅንሰ ሀሳቦች መረዳታቸውን ያረጋግጡ<br>☞ **ክትትል**<br>✍ ተማሪዎቹ የዕለቱን ርዕስ መገንዘባቸውን ለማወቅ በተናጠል የተለያዩ ጥያቄዎች በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ ። |

**የተግባር 3 መልስ**

ተማሪዎችን በቡድን ከከፈሉ በኋላ በመማሪያ መጽሃፋቸው ላይ የተፃፈውን ታሪክ ያንብቡላቸው፡፡ እያንዳንዱ ቡድን ከተነበበው ታሪክ ምን እንደተረዱ እንዲገልፁ ያድርጉ፡ ፡በስተመጨረሻም የታሪኩን ጭብጥ ለተማሪዎች ያስረዱ፡፡

እንደ ፌዴራላዊ የመንግስት አወቃቀር መርህ የስልጣን ክፍፍል በፌዴራል እና በክልል መንግስታት መካከል መኖሩን ያሳያል፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ እንደተቀመጠው ግን የፌዴራል መንግስት ህግን በመተላለፍ በክልል መንግስታት ጣልቃ መግባቱን ያሳያል፡፡

## ይዘት 5፡ የመንግስት ስርዓቶች

**ተማሪዎች ሊጎናፃፉ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፡-**

- የተለያዩ የመንግስት ስርዓቶችን ይገልፃሉ፤
- የመንግስት ስርዓት ፅንሰ ሀሳቦችን ይገልፃሉ፡፡

## ማብራሪያ

በዚህ ርዕስ ሥር ተማሪዎች የመንግስት ስርዓትን መግለፅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመንግስት ስርዓት በአስፈጻሚው እና በሕግ አውጪው የመንግስት አካላት መካከል ያለውን ግንኙነት ያመለክታል፡፡ በዚህ ዓለም ላይ ሶስት አይነት የመንግስት ስርዓቶች አሉ፡፡ እነሱም ፕሬዚዳንታዊ፣ ፓርላሜንታዊ እና ድብልቅ ተብለው ይታወቃሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ሂደት

| ተ.ቁ | ማዕቀፍ | ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህረት መርጃ መሳሪያዎች | ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ፣ እርሳሶች፣ ሥዕሎች፣ እና ሠንጠረዥ |
| 2 | የማስተማር ስልቶች | የማነቃቂያ ጥያቄ፣ መግቢያ እና ማብራሪያ ፣ የግል ስራዎች፣ የቡድን ውይይት እና አቀራረብ |
| 3 | የማጣቀሻ ቁሳቁስ | በመንግስት ስርዓቶች ላይ የተፃፉ መጣጥፎች እና መጽሔቶች፣ http://www.shivajicollege.ac.in |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | ቅድመ ዝግጅት | ✍ የርዕስ እቅድን ማዘጋጀት እና በክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት ማቀናጀት<br>✍ የተለያዩ የማጣቀሻ መፅሕፍት በማንበብ በደንብ መዘገጀትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት |
| 5 | የርዕስ<br>አቀራረብ | የትምህርቱ መግቢያ<br>✍ የመማር ማስተማር ሂደት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው፡፡<br>✍ የዕለቱን ርዕስ ቀለል በለ አቀራረብ እና በጥያቄ ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡<br>ለምሳሌ፡- የመንግስት ስርዓት ምንድንነው? |
| | | የትምህርቱ አካል<br>✍ በመንግስት ስርዓት ላይ እውቀት መፍጠር<br>✍ ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎች በማስታዋሻ ደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ ሰፊ ማብራሪያዎችን ያድርጉ |
| | | ሚዘና እና ግምገማ<br>✍ የትምህርቱን ማጠቃለያ ማድረግ፣ የክትትል ስራዎችን እና ጥያቄዎችን በቃል ማቅረብ፣ አስፈላጊ ከሆነ የክፍል ፈተና መስጠት ይችላሉ፡፡<br>✍ እነዚህም የግምገማ ጥያቄዎች የትምህርቱ ዓላማዎች ምን ያህል እንደተሳኩ ለመገምገም ይረዱዎታል<br>☞ **ግምገማ**<br>✍ በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪዎችዎ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የትምህርቱን አስፈላጊ ፅንሰ ሀሳቦች መረዳታቸውን ያረጋግጡ<br>☞ **ክትትል**<br>✍ ተማሪዎቹ የዕለቱን ርዕስ መገንዘባቸውን ለማወቅ በተናጠል የተለያዩ ጥያቄዎች በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ ፡፡ |

# ይዘት 6፡ ፓርላሜንታዊ የመንግስት ስርዓት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናፃፉ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፡-

- የፓርላሜንታዊ የመንግስት ስርዓት ፅንሰ ሀሳብን ይገልፃሉ፤
- የፓርላሜንታዊ ስርዓት መንግስት ባህሪያትን ይለያሉ፡፡

## ማብራሪያ

በዚህ ርዕስ ሥር ተማሪዎች የፓርላሜንታዊ የመንግስት ስርዓትን መግለፅ አለባቸው። በጠቅላይ ሚንስትር የሚመራው የመንግስት ስርዓት የፓርላሜንታዊ የመንግስት ስርዓት ይባላል፡፡ በፓርላሜንታዊ የመንግስት ስርዓት ውስጥ ከፍተኛ ድምፅ ያገኘው ፓርቲ መንግሥት መመስረት ይችላል። በዚህ ስርዓት ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾመው በፓርቲው ወይም በቅንጅቱ መሪ ስሆን ማንኛውም ፓርቲ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመወዳደር የፓርላማውን ወንበር መጋራት ይችላሉ፡፡ በፓርላሜንታዊ የመንግስት ስርዓት የስራ አስፈፃሚ አባላት ተጠርነታቸው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፡፡ ገዥው ፓርቲ ወይም ፓርላማው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ እምነት ከጣ ከስልጣን ሊያስነሳ ይችላል።

## የመማር ማስተማር ሂደት

| ተ.ቁ | ማዕቀፍ | ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህረት መርጃ መሳሪያዎች | ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ፣ እርሳሶች፣ ሥዕሎች፣ እና የገበታ ወረቀት |
| 2 | የማስተማር ስልቶች | የማነቃቂያ ጥያቄ፣ መግቢያ እና ማብራሪያ ፣ የግል ስራዎች, የቡድን ውይይት እና አቀራረብ |
| 3 | የማጣቀሻ ቁሳቁስ | በፓርላሜንታዊ ስርዓቶች ላይ የተፃፉ መጣጥፎች እና መጽሔቶች |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | ቅድመ ዝግጅት | ✍ የርዕስ እቅድን ማዘጋጀት እና በክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት ማቀናጀት<br>✍ የተለያዩ የማጣቀሻ መፅሕፍት በማንበብ በደንብ መዘገጀትና የትምህረት የመርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት |
| 5 | የርዕስ<br>አቀራረብ | የትምህርቱ መግቢያ<br>✍ የመማር ማስተማር ሂደት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው፡፡<br>✍ የዕለቱን ርዕስ ቀለል በለ አቀራረብ እና በጥያቄ ልጀምሩ ይችላሉ፡፡ |
| | | የትምህርቱ አካል<br>✍ በፓርላሜንታዊ የመንግስት ስርዓት ላይ እውቀት መፍጠር<br>✍ ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎች በማስታዋሻ ደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ እንዲወያዩ ከደረጉ በኋላ ሰፊ ማብራሪያዎችን ያድርጉ |
| | | ሚዘና እና ግምገማ<br>✍ የትምህርቱን ማጠቃለያ ማድረግ፣ የክትትል ስራዎችን እና ጥያቄዎችን በቃል ማቅረብ፣ አስፈላጊ ከሆነ የክፍል ፈተና መስጠት ይችላሉ፡፡<br>✍ እነዚህም የግምገማ ጥያቄዎች የትምህርቱ ዓላማዎች ምን ያህል እንደተሳኩ ለመገምገም ይረዱዎታል<br>☞ **ግምገማ**<br>✍ በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪዎችዎ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የትምህርቱን አስፈላጊ ፅንሰ ሀሳቦች መረዳታቸውን ያረጋግጡ<br>☞ **ክትትል**<br>✍ ተማሪዎቹ የዕለቱን ርዕስ መገንዘባቸውን ለማወቅ በተናጥል የተለያዩ ጥያቄዎች በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ ። |

# ይዘት 7፡ ፕሬዝዳንታዊ የመንግስት ስርዓት

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናፃፉ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፡-

- የፕሬዝዳንታዊ መንግስት ስርዓት ምንነትን ይገልፃሉ፤
- የፕሬዚዳንታዊ መንግስት ስርዓት ባህሪያትን ይለያሉ፡፡

## ማብራሪያ

በዚህ ርዕስ ሥር ተማሪዎች የፕሬዝዳንታዊ የመንግስት ስርዓት ማብራራት ይጠበቅባቸዋል። በፕሬዚዳንታዊ ሥርዓት ውስጥ ፕሬዚዳንቱ/ቷ በቀጥታ በህዝብ የሚመረጥ ስሆን ተጠሪነቱም ለህዝብ ይሆናል፡፡ፕሬዝዳንታዊ ስርዓት ፕሬዝዳንቱ የሀገር እና የመንግስት ርዕሰ መስተዳድር የሆነበት የመንግስት ስርዓት ነው። በዚህ ስርዓት ውስጥ ሶስቱም የመንገስት አካለት እራሳቸውን የቻሉ ናቸው፡፡

## የመማር ማስተማር ሂደት

| ተ.ቁ | ማዕቀፍ | ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህረት መርጃ መሳሪያዎች | ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ፣ እርሳሶች፣ ሥዕሎች፣ እና የገበታ ወረቀት |
| 2 | የማስተማር ስልቶች | የማነቃቂያ ጥያቄ፣ መግቢያ እና ማብራሪያ ፣ የግል ስራዎች, የቡድን ውይይት እና አቀራረብ |
| 3 | የማጣቀሻ ቁሳቁስ | በፕሬዝዳንታዊ መንግስት ስርዓት ላይ የተፃፉ መጣጥፎች እና መጽሔቶች |
| 4 | ቅድመ ዝግጅት | • የርዕስ እቅድን ማዘጋጀት እና በክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት ማቀናጀት<br>• የተለያዩ የማጣቀሻ መፅሕፍት በማንበብ በደንብ መዘገጀትና የትምህርት የመርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት |
| 5 | የርዕስ | የትምህርቱ መግቢያ |

| | | |
|---|---|---|
| | አቀራረብ | ✍ የመማር ማስተማር ሂደት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው፡፡<br>✍ የዕለቱን ርዕስ ቀለል በለ አቀራረብ እና በጥያቄ ልጀምሩ ይችላሉ፡፡ |
| | | የትምህርቱ አካል<br>✍ በፕሬዝዳንታዊ መንግስት ስርዓት ላይ እውቀት መፍጠር<br>✍ ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎች በማስታዋሻ ደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ እንዲወያዩ ከደረጉ በኋላ ሰፊ ማብራሪያዎችን ያድርጉ |
| | | ሚዘና እና ግምገማ<br>✍ የትምህርቱን ማጠቃለያ ማድረግ፣ የክትትል ስራዎችን እና ጥያቄዎችን በቃል ማቅረብ፣ አስፈላጊ ከሆነ የክፍል ፈተና መስጠት ይችላሉ፡፡<br>✍ እነዚህም የግምገማ ጥያቄዎች የትምህርቱ ዓላማዎች ምን ያህል እንደተሳኩ ለመገምገም ይረዱዎታል<br>☞ **ግምገማ**<br>✍ በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪዎችዎ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የትምህርቱን አስፈላጊ ፅንሰ ሀሳቦች መረዳታቸውን ያረጋግጡ<br>☞ **ክትትል**<br>✍ ተማሪዎቹ የዕለቱን ርዕስ መገንዘባቸውን ለማወቅ በተናጥል የተለያዩ ጥያቄዎች በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ ። |

# ይዘት 8፡ ድብልቅ የመንግስት ስርዓት

ተማሪዎች ሊጎናፀፉ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፡-

- የድብልቅ መንግስትን ስርዓት ምንነትን ይገልፃሉ፤
- የድብልቅ መንግስትን ስርዓት ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፡፡

## ማብራሪያ

በዚህ የርዕስ ይዘት ውስጥ ተማሪዎች ስለ ድብልቅ የመንግስት ስርዓት ይማራሉ፡፡ በድብልቅ የመንግስት ስርዓት ውስጥ የፕሬዝደንት እና የጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣን በጋር ሥራ ላይ የሚውልበት ስርዓት ነው፡፡ ፕሬዝደንቱ/ቷን ለብቻ በመመረጥ የሥራ አስፈፃሚነት ስልጣን ያለው ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደግም በህግ አውጪ አካል ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ይኖረዋል፡፡

## የመማር ማስተማር ሂደት

| ተ.ቁ | ማዕቀፍ | ተግባራት |
|---|---|---|
| 1 | የትምህረት መርጃ መሳሪያዎች | ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ፣ እርሳሶች፣ ሥዕሎች፣ እና ሠንጠረዥ |
| 2 | የማስተማር ስልቶች | የማነቃቂያ ጥያቄ፣ መግቢያ እና ማብራሪያ ፣ የግል ስራዎች, የቡድን ውይይት እና አቀራረብ |
| 3 | የማጣቀሻ ቁሳቁስ | በድብልቅ መንግስት ስርዓት ላይ የተፃፉ መጣጥፎች እና መጽሔቶች |
| 4 | ቅድመ ዝግጅት | - የርዕስ እቅድን ማዘጋጀት እና በክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት ማቀናጀት<br>- የተለያዩ የማጣቀሻ መፅሕፍት በማንበብ በደንብ መዘገጀትና የትምህረት የመርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት |
| 5 | የርዕስ አቀራረብ | የትምህርቱ መግቢያ<br>- የመማር ማስተማር ሂደት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ✍ የዕለቱን ርዕስ ቀለል በለ አቀራረብ እና በጥያቄ ልጀምሩ ይችላሉ፡፡ |
| | | የትምህርቱ አካል<br>✍ በድብልቅ መንግስት ስርዓት ላይ እውቀት መፍጠር<br>✍ ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎች በማስታዋሻ ደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ ሰፊ ማብራሪያዎችን ያድርጉ |
| | | ሚዘና እና ግምገማ<br>✍ የትምህርቱን ማጠቃለያ ማድረግ፣ የክትትል ስራዎችን እና ጥያቄዎችን በቃል ማቅረብ፣ አስፈላጊ ከሆነ የክፍል ፈተና መስጠት ይችላሉ፡፡<br>✍ እነዚህም የግምገማ ጥያቄዎች የትምህርቱ ዓላማዎች ምን ያህል እንደተሳኩ ለመገምገም ይረዱዎታል<br>☞ **ግምገማ**<br>✍ በትምህርቱ መጨረሻ ተማሪዎችዎ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የትምህርቱን አስፈላጊ ፅንሰ ሀሳቦች መረዳታቸውን ያረጋግጡ<br>☞ **ክትትል**<br>✍ ተማሪዎቹ የዕለቱን ርዕስ መገንዘባቸውን ለማወቅ በተናጠል የተለያዩ ጥያቄዎች በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ ። |

## ይዘት 9፡ በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካከል ያለው ግንኙነት እና ልዩነት

**ተማሪዎች ሊጎናፀፉ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፡-**

- በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካከል ያለውን ግንኙነት ይገልፃሉ፤
- በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካከል ያለውን ልነት ይገልፃሉ፡፡

**ማብራሪያ**

